لجنة توزيع المطبوعات الدينية على الحجاج والمعتمرين

ኢሕራም ቦታዎች

ሐጅና ዑምራ አፈፃፀም

ሊሒጃ ስምንት (የውመል ተርዊያ)

ልሒጃ ዘጠኝ የአረፋ ቀን

ሙዝደሊፋ

ርድ ቀን (የውመል ነሕር)

ያመል ተሽሪቅ

ቶችን የሚመለከት መመርያ

ስፈላጊ ጥያቄና መልስ


መስጂደል ነበዊ ዚያራ

ዓ

# የሐጅና ዑምራ ማብራሪያ


አዘጋጅና አቅራቢ

በሼኽ ጠላል ቢን አህመድ አል አቂል

መቅደም በክቡር ሼኽ ሳልሕ ዓብድል
ዓዚዝ መሐመድ አል አሽይኽ
በሳዑዲ ዓረቢያ የእስልምና የአውቃፍ
የዳዕዋና የኢርሻድ ሚኒስቲር

بسم الله الرحمن الرحيم

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

# የሐጅና ዑምራ ማብራሪያ




አዘጋጅና አቅራቢ በሼኽ ጠላል ቢን አህመድ አል አቂል

ትርጉም ሰይፈዲን ሐበሻ ያሲን - ከጅዳ የዳዕዋ ማዕከል

እርምት በዶክተር ዓብድልጀሊል ሐሰን አሩሲ

## መልዕክቱ የተውጣጣባቸው ኪታቦች

- ተሕቂቅ ወልኢዷሕ ........................ በሼኽ ዓብዱል ዐዚዝ ቢን ባዝ
- ቢፉቱል ሐጅ ወል ዑምራ ........ በሼኽ መሐመድ ቢን ኡሰይሚን
- አሕካም ተኹተስ ቢል ሙዕሚናት......በሼኽ ዶ/ ሳሊሀ ቢን ፈውዛን
- ኪታብ ሑስኑል ሙስሊም........... በሼኽ ሰዒድ ቢን ወሀፍ ቀሕጣኒ
- ፈታዋ ለጅና ዳኢማ....................ለጅና ዳኢማ ሊል ቡሑስ ዒልሚያ


ⓒ طلال بن أحمد العقيل ، ١٤٢٣هـ

فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر

العقيل ، طلال بن أحمد
دليل الحاج والمعتمر - جدة ،
٨٠ صفحة ، ١٢×١٧سم
ردمك : ٩-٩٦٤-٤١-٩٩٦٠
١ - الحج - مناسك ٢ - العمرة أ - العنوان
ديوي ٢٥٢,٥ ٢٣/٣٩١٧

رقم الإيداع : ٢٣/٣٩١٧
ردمك : ٩-٩٦٤-٤١-٩٩٦٠



حقوق الطبع محفوظة للمؤلف



هاتف ٦٣٩١٨٠٠ فاكس ٦٩٨٦٣٥٥ جوال ٠٥٥٦٤٨٦٥٩
ص. ب ١٨٤٥٥ جدة ٢١٤١٥
المملكة العربية السعودية

أعوذ بالله من الشيطان الرجيم

## የሐጅና ዑምራ ማብራርያ

ٱلْحَجُّ أَشْهُرٌ مَّعْلُومَٰتٌ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلْحَجَّ فَلَا رَفَثَ
وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِى ٱلْحَجِّ وَمَا تَفْعَلُوا۟ مِنْ خَيْرٍ
يَعْلَمْهُ ٱللَّهُ وَتَزَوَّدُوا۟ فَإِنَّ خَيْرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقْوَىٰ وَٱتَّقُونِ
يَٰٓأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٧﴾ لَيْسَ عَلَيْكُمْ جُنَاحٌ أَن
تَبْتَغُوا۟ فَضْلًا مِّن رَّبِّكُمْ فَإِذَآ أَفَضْتُم مِّنْ
عَرَفَٰتٍ فَٱذْكُرُوا۟ ٱللَّهَ عِندَ ٱلْمَشْعَرِ ٱلْحَرَامِ
وَٱذْكُرُوهُ كَمَا هَدَىٰكُمْ وَإِن كُنتُم مِّن قَبْلِهِۦ
لَمِنَ ٱلضَّآلِّينَ ﴿١٩٨﴾ ثُمَّ أَفِيضُوا۟ مِنْ حَيْثُ أَفَاضَ
ٱلنَّاسُ وَٱسْتَغْفِرُوا۟ ٱللَّهَ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١٩٩﴾
فَإِذَا قَضَيْتُم مَّنَٰسِكَكُمْ فَٱذْكُرُوا۟ ٱللَّهَ كَذِكْرِكُمْ
ءَابَآءَكُمْ أَوْ أَشَدَّ ذِكْرًا فَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن
يَقُولُ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا وَمَا لَهُۥ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنْ
خَلَٰقٍ ﴿٢٠٠﴾ وَمِنْهُم مَّن يَقُولُ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا
حَسَنَةً وَفِى ٱلْءَاخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿٢٠١﴾
أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ نَصِيبٌ مِّمَّا كَسَبُوا۟ وَٱللَّهُ سَرِيعُ ٱلْحِسَابِ ﴿٢٠٢﴾

አል በቀራህ 197 – 202

# መቅደም

بسم الله الرحمن الرحيم

አቅማቸው በፈቀዱ ባሮቹ ላይ ወደ አላህ ቤት ሐረም ሐጅን ግዴታ አድርጎ ሐጃቸው ለተዋጣላቸው ምንዳውን የወንጀልንና የጥፋት ማበሻ ያደረገው አላህ ምስጋና ይገባው። ለአላህ ጥሪ ምላሽ በመስጠት ለበይክ ብለው ጠዋፍና ሰዕይ ካደረጉት ሁሉ በላጭ በሆኑትና በተመረጡት ነብዩ መሐመድ ሰላምና ሰላት ለሳቸው ፣ ለቤተሰቦቻቸው ፣ ለሰሐቦቻቸውና በሳቸው እየተዳኝ በመልካም ለተከተላቸው ሁሉ ይሁን ።

በመቀጠል :- ውድ ወንድሜ ሐጅ ሆይ እንኳን ወደዚህ ወደተከበረው ሃገር በሰላም መጣህ እያልኩኝ ሐጅና ዑምራህ አላህ በሚፈልገው መልኩ እንዲሆንና ሐጅህንም አላህ ተቀብሎት በመልካም ሥራ ሚዛኖችህ ላይ እንዲያደርግልህ እለምነዋለሁ ።
ወደ አላህ ቤት ያቀናህ ወንድሜ ሆይ ለሁሉም ተሳፋሪ መሪና ለሁሉም ጉዞ ፋና እንዳለው ሁሉ የሐጃጆችም መሪ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሲሆኑ የጉዞውም ፋና መመርያቸውና ሱናቸው ነው ለዚህም ነው እሳቸው የሐጅ (ሥራዎቻችሁን ከኔ ውሰዱ) ያሉት ።
ስለዚህ ወደ አላህ ቤት ለሐጅና ዑምራ ያቀና ሁሉ ታአማኒነት ካላቸው ስለ ሐጅና ዑምራ የሚያብራሩ መፅሐፎች አማካኝነት ስለ ሐጅና ዑምራ ማወቅ ሲኖርበት በሚያምታቱ ጉዳዮች የዕውቀት ባለቤቶችን መጠየቅ ይገባዋል።

የተከበርከው ሐጅ ሆይ ይህ ፊትለፊትህ የምታየው መፅሐፍ ማብራሪያው ግልፅ ሆኖ በስዕላዊ መግለጫ ተደግፎ በአዲስ መልክ የተዘጋጀ በመሆኑ የሐጅንና ዑምራ አፈፃፀም በቀላሉ ልትረዳበት ትችላለህ። ስለዚህ ይህቺን መፅሐፍ የሐጅና ዑምራህን አፈፃፀም መሪ አድርገህ እየተጠቀምክ ባልገቡህ ጉዳዮች ላይ በሳዑዲ አረቢያ የእስልምና ጉዳዮች ሚኒስቴር ሃላፊነቱን በመውሰድ የምትፈልገውን ሁሉ ሊያገለግልህ ተዘጋጅቷል ይኸውም ሐጅ ላይ በተለያዩ ጣቢያዎች ላይ ባሉ ትናንሽ ቤቶች ውስጥ የምትጠይቃቸው የዕውቀት ባለቤቶችን ታገኛለህ አላህም በቁርአኑ :-

فَسْـَٔلُوٓاْ أَهْلَ ٱلذِّكْرِ إِن كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ

ትርጉም ((.. የማታውቁትም ብትኾኑ የዕውቀትን ባለቤቶች ጠይቁ)) ብሏልና :: አል ነሕል - 43

ከማጠቃለሌ በፊት ይህን የሐጅና የዑምራ መመርያ መፅሐፍ ላዘጋጀው ለወንድሜ ለሼኽ ጠላል ቢን አህመድ አል ዓቂል የከበረ ምስጋናዬን እያቀረብኩ በዚህ መፅሐፍም ሆነ በሌላ መስክ ለሚያደርጋቸው ጥረቶች በመልካም ሥራው ሚዛን ላይ እንዲሰፍርለት አላህን እለምነዋለሁ፡ በተጨማሪ ለሐጃጆች የዲን መልዕክት የያዙ ሕትመቶችን የሚያድለው ጅዳ የሚገኙት የሼኽ ጠላል የሥራ ባልደረቦቹና ባጠቃላይ ለኮሚቴው ለዚህ ለተባረከው ሥራቸው አላህ ምንዳውን ይስጣቸው እላለሁ ::

የአላህ ቤት እንግዳ የሆንክ ሐጅ ሆይ ሌላው የማስተላልፈው ጉዳይ አንተንም ሆነ እራሴን አደራ የምለው ይህንን ውድ ጊዜህን በመሸማት በእንግድነት ወደቀረብከው ጌታህ የሚወደውን ሥራ ብቻ በመሥራት የተከበረው ቤቱን በማተለቅ አላህን ከሚያስቆጡ ሥራዎች መቆጠብ ይገባሃል:: አላህም በቁርአኑ ሲያስጠነቅቅ:-

وَمَن يُرِدْ فِيهِ بِإِلْحَادٍۭ بِظُلْمٍ نُّذِقْهُ مِنْ عَذَابٍ أَلِيمٍ

(الحج 025)

ትርጉም ((.. በሱም ውስጥ (በመስጂደል ሐረም ውስጥ ከትክክለኛ ው መንገድ) በመዘንበል በዳይ ሆኖ (ማንኛውንም ነገር) የሚፈልግ ሰው ከአሳማሚ ቅጣት እናቀምሰዋለን)) ይላል:: አልሐጅ - 25
በመጨረሻ ሐጅህ የተዋጣለት (መብሩር) ሥራህ የሚያስመሰግንህ (መሽኩር) ወንጀልህም የተማረ እንዲሆን አላህን እለምነዋለሁ አላህም ከሁሉም በላይ አዋቂ ነው (አላሁ አዕለም)::

ወሰላም አለይኩም ወራህመቱሏሂ ወበረካቱሁ

በሳዑዲ ዓረቢያ የእስልምና ጉዳዮች የወቅፍ የዳዕዋና የኢርሻድ ሚኒስቴር:- ሷሊሕ ዓብዱልዓዚዝ ቢን መሐመድ አል አሸይኽ::

# ጥንታዊው ቤት (ሐረም)

ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ምስጋና ይገባው ሰላትና ሰላም ለነብዩ መሐመድ ለቤተሰቦቻቸውና ለባልደረቦቻቸው ይሁን።

**በመካ ከተማ ሐረም መስጊድ ውስጥ የሚገኘው ካዕባ የአላህ ጥንታዊ ቤት ነው።**

ካዕባ ሙስሊሞች የትም ቦታ ቢሆኑ ከልባቸው የማይጠፋ ሥፍራ ሲሆን ፊቶችና ልቦቻቸውም በቀን አምስት ጊዜ ወደ ካዕባ አዙረው ለአንዱ አምላክ ለአላህ ተናንሰውና ፈርተው ይሰግዳሉ ።

ጥንታዊው ቤት (ካዕባ) በነብዩ ኢብራሂም ከተገነባበት ጊዜ ጀምሮ ሙስሊሞች በተከበረው ቤት ዙርያ ጠዋፍ ለማድረግና የሐጅ ሥርዓትን ለማከናወን ከሚኖሩበት እሩቅ ሸለቆ አቋርጠው ወደ መካ ይጎርፋሉ ።

ሰዎች ከባዕድ አምልኮ ተላቀው የፈጠራቸውን አንድ አምላክ አላህን ብቻ ፍፁም በሆነ በትክክለኛ እምነት በኢስላም ሊገዙት የመጀመርያው ጥንታዊው ቤት (ካዕባ) ተመሰረተ አላህም በቁርአን ሊገልፀው ፦

إِنَّ أَوَّلَ بَيْتٍ وُضِعَ لِلنَّاسِ لَلَّذِي بِبَكَّةَ مُبَارَكًا وَهُدًى لِّلْعَالَمِينَ ﴿٩٦﴾
فِيهِ آيَاتٌ بَيِّنَاتٌ مَّقَامُ إِبْرَاهِيمَ وَمَن دَخَلَهُ كَانَ آمِنًا وَلِلَّهِ عَلَى النَّاسِ
حِجُّ الْبَيْتِ مَنِ اسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ اللَّهَ غَنِيٌّ عَنِ الْعَالَمِينَ

ትርጉም ((ለሰዎች (መጸለያ) መጀመርያ የተኖረው ቤት ብሩክና ለዓለማት ሁሉ መመርያ ሲሆን ያ በበካህ (በመካ) ያለው ነው ! በውስጡም ግልፅ የኾኑ ታምራቶች የኢብራሂም መቆሚያም አለ (ውስጡም) የገባ ስው ፀጥተኛ ይሆናል (ሰላምን ያገኛል) ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መሄድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።)

አል ኢምራን ፤ 96 – 97

# የኢስላም መሠረቶች

የተከበራችሁ ሙስሊሞች
በቡኻሪና ሙስሊም ሐዲስ ከነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንደተረጋገጠው

« ኢስላም በአምስት መዓዘኖች ተገንባ » እነሱም

ከዚህ የምንረዳው ሐጅ ከኢስላም መሰረቶች አንዱ በመሆኑ አንድ ሙስሊም አቅሙ እያለው ሐጅ እስካላደረገ ድረስ እስልምናው ሙሉ አይሆንለትም።
የአላህ እዝነቱ ሆኖ ሐጅ ለአንድ ሙስሊም በዕድሜ ልኩ ከአንድ ጊዜ በላይ ግዴታ አይሆንበትም።
ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሐጅ ግዴታ (ፈርድ) መሆኑን ሲናገሩ አንድ ሰሐባ በየአመቱ ነው ? ብሎ ጠየቃቸው
እሳቸውም (ሐጅ አንዴ ነው የደገመ ትርፍ (ተጠውዕ) ነው) አሉት ሐዲስ ስሒሕ
ሐጅ ሲደረግ ከይዩልኝ እና ከይስሙልኝ ተጠንቅቆ ፍፁም ለአላህ መሆን አለበት።
አላህም በሐዲሰል ቁድስ :-
( እኔ ሲያሻርኩብኝ እቀናለሁ አንድ ሥራ ሰርቶ በእኔ ላይ ያሻረከ ከነሽርኩ እተወዋለሁ ብሎዋል )
ሐጅ ሲደረግ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ባሳዩት መሠረት መሆን አለበት ።
እኛም ሙስሊም ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን የምንመክረው ለሐጅ ጉዞ ከመነሳታቸው በፊት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሐጅ እንዴት ነበር ያደረጉት? ብለው በደንብ መጠየቅና ማወቅ አለባቸው ።
ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳዘዙት

(የሐጅና ዑምራ አፈፃፀም ከኔ ውሰዱ) ብለዋል።

ላኢላሃ ኢለላህ መሐመድ ረሱሉላህ ብሎ መመስከር

የአምስት ወቅት ሰላት . መስገድ

ከገንዘብ ላይ ዘካ ማውጣት

የረመዳንን ወር መፆም

ወደ አላህ ቤት መካሐጅ ማድረግ፡ ናቸው

# የጉዞ ሥነ ሥርዓት

1. ሐጅና ዑምራ ለማድረግ የተነሳ ኒያውን አስተካክሎ ፍፁም ወደ አላህ ሊቃረብበት መሆን አለበት ሐጅ ሲነየት ለዱንያ ፣ለጉራ ፣ ሐጂ ለመባል ፣ ለይዩልኝ እና ለይስሙልኝ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

2. ለጉዞ የተነሳ ሰው ምንግዜም ቢሆን በንብረትና በዕዳ ጉዳይ ኑዛዜ መፃፍ ይገባዋል የሰዎችን የአደራ ንብረት የተቀበለ ከሆነ እራሱ ዘንድ እንዲቀመጥ ወይንም እንዲመልስላቸው ለባለ አደራዎቹ ማስመረጥ አለበት።

3. ባለፈው በሰራቸው ወንጀሎች ተፀፅቶ መቶበትና ደግሞ ወንጀል ላለመፈፀም ፅኑ የሆነ አቋም መያዝ አለበት ።

4. ሰዎችን በድሏቸው ከሆነ ይቅርታ መጠየቅ ፣ ንብረታቸውን በግፍ የወሰደ ከሆነ መመለስ አለበት ።

5. ለሐጅና ዑምራ የሚያወጣው ወጪ ፍፁም ሐላል መሆን አለበት ምክንያቱም አላህ ከጉድለት ሁሉ የጠራ በመሆኑ የጠራን ሥራ ብቻ ነው የሚቀበለው ።

6. ከሁሉም ወንጀሎች መራቅ ይጠበቅበታል ይኸውም ፡- በምላሱም መጥፎ በመናገርና በሰውነቱ ግፍያ በመፍጠር ሰውን ያለመበደል ፣ ከሃሜትና ከጊደኛ ጋር ከመጨቃጨቅ መቆጠብ ፣ ሁሉንም አይነት ውሸት መራቅ በተለይ በዲን ጉዳይ በማያውቀው ነገር አላህ እንዲህ ብሏል ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል ብሎ መዋሸት ትልቅ ወንጀል ስለሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

# የጉዞ ሥነ ሥርዓት

7. ሐጃጆች በሐጅና ዑምራ ዙሪያ ባሉ መመሪያዎች እርስ በርስ መስማማት አለባቸው።

8. መንገደኛ ተጓዥ ኢስላም ግዴታ ያደረገውን ሁሉ መፈፀም አለበት ፦ በተለይ ሰላትን በወቅቱ በጀምዓ መስገድ ፣ የቻለውን ያህል ቁርአን መቅራት ፣ ዚክር ማብዛት ፣ ዱዓ ማድረግ ፣ በንግግርም ሆነ በተግባር ለሰዎች መልካም ፀባይ ማሳየት ፣ የተቸገረን መርዳት ፣ ለሙስሊሞች መራራት ፣ ለድሃ መመፅወት ፣ በመልካም እያዘዙ በመጥፎ መከልከል የመሳሰሉት ሁሉ የሙስሊም ፀባዮቹ ናቸው።

9. መንገደኛ ከጉዞው በፊት በጥሩ ኢስላማዊ ሥነ - ምግባር የታነፁ ጓደኞች መምረጥ አለበት።

10. ሙስሊም መንገደኛ ፍፁም የሆነ መልካም ፀባይ መላበስ አለበት ይኸውም ፦ ትዕግስት ፣ ተበድሎ ማለፍ ፣ ይቅር መባባል ፣ መቻቻል ፣ አመለ ቀዝቃዛ መሆን ፣ ችኩል ያለመሆን ፣ መተናነስ ፣ መለገስ ፣ ንቁና ትጉህ መሆን ፣ መተዛዘን ፣ ጥንቁቅ ፣ ጨዋ ፣ ታማኝ ፣ ሥርዓት ያለው ፣ አላህን የሚፈራ ፡ መሆን ይጠበቅበታል።

11. መንገደኛ ሙስሊም ከቤቱ ሲወጣ አላህ ባዘዘው መሰረት ለቤተሰቦቹ አላህን እንዲፈሩ አደራ ማለት አለበት ።

12. መንገደኛ ከረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የተገኙትን የመንገደኛ ዚክሮችና ዱዓዎችን በተቻለ መጠን በቃሉ መያዝ ይወደዳል።

ገፅ 77 ይመልከቱ

# አል ኢሕራም
## (ሐጅ ወይንም ዑምራ መነየት)

ኢሕራም የሐጅና ዑምራ የመጀመርያ ሥራ ነው
ኢህራም ወደ ሐጅና ዑምራ ሥራ (ኑሱክ) ለመግባት የሚደረግ ኒያ ነው ወቅቱም ለዑምራ አመቱን ሙሉ ሲሆን ለሐጅ ግን ኒያ የሚደረገው

የሸዋልና ዙልቂዒዳ ሙሉ ወሮችና በዙልሒጃ አሥር ቀኖች ናቸው:: (ዙልሂጃ አሥር ሌሊቱ ብቻ ነው በሐጅ ጊዜያቶች ውስጥ የሚጠቃለለው)

የሐጅና ዑምራ ሥራ የሚጀመረው ከተወሰኑት ክልሎች (ሚቃት) ላይ የኢሕራም ልብስ ለብሶ ኒያ በማድረግ ነው ::

ሐጅና ዑምራ ለማድረግ የፈለገ በመርከብም ሆነ በሌላ መጓጓዣ ተጉዞ የኢሕራም ክልሎች (ሚቃት) እንደደረሰ መጀመርያ ከተሳካለት ገላውን ታጥቦና ተበጃጅቶ ወንድ ነጭ የሆነ ብትን ጨርቆች በማዘጋጀት አንዱን ከወገብ በታች አሸርጦ አንደኛውን ከወገብ በላይ አጣፍቶ ይለብሳል :: ለሴት ግን ለኢሕራም የተለየ ልብስ የላትም የሰውነቷን ቅርፅ የማያሳይ ከእጇና ከፊቷ በስተቀር ሙሉ ሰውነቷን የሚሸፍን የፈለገችውን አይነትና መልክ ያለው ልብስ መልበስ ትችላለች ባዕድ ወንድ መሀል ግን ፊቷን በጨርቅ ጣል አድርጋ መሸፈን አለባት::

በመቀጠልም ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ለሐጅ ወይንም ለዑምራ በሚከተለው መልኩ ይነይታሉ

ለበይክ ማለት ከተጀመረ በኋላ ወደ ሐጅና ዑምራ ሥራ (ኑሱክ) ተገባ ማለት ነው::

– ሐጃጆች የሚጓዙት በባሕር ወይንም በአውሮፕላን ከሆነ እንደተለመደው አብራሪዎች የሚቃት ክልል መድረሳቸውን ይናገራሉ በዚህን ጊዜ ሐጃጆች የኢሕራም ልብሳቸውን ለብሰው ተልቢያ በማለት ኢሕራም ያደርጋሉ (ኢሕራም ማለት ወደ ሐጅና ዑምራ ሥራ ለመግባት መነየት ወይንም መወሰን ማለት ነው) ሐጃጆች ከፈለጉ ከቤታቸው ሲወጡ የኢሕራም ልብስ ለብሰው ሚቃት ክልል ሲደርሱ ተልቢያ በማድረግ ወደ ሐጅና ዑምራ ሥራ መግባት ይችላሉ ::

በተልቢያ ጊዜ ወንዶች ድምፃቸውን ከፍ ሲያደርጉ ሴቶች ግን ድምፃቸውን ለራሳቸው ብቻ እንዲሰማ አድርገው ተልቢያ ይላሉ::

ለበይክ ዑምራ - ዑምራ ብቻ ለሚያደርግ

ሙተመቱዕ.ዑምራና ሐጅ ለየብቻ ለማድረግ - ለበይክ ዑምራ ሙተመቲዓን ቢሃ ኢለል ሐጅ ትርጉም (ከዑምራ በኋላ ኢሕራሜን ፈትቼ ሐጅም ላደርግ ማለት ነው)

አል ቃሪን (ለበይክ ዑምራ ወሐጅ) ዑምራና ሐጅ አንድ ላይ ላደርግ ማለት ነው

አል ሙፍሪድ ለበይክ ሐጀን ትርጉም ሐጅ ላደርግ

# ከኢሕራም በፊት

**ከኢሕራም በፊት የሚከተሉትን ማከናወን ይወደዳል**

1. ጥፍርን መቁረጥ ፣ በብብትና በብልት አካባቢ ያለን ፀጉር መላጨት ወንዶች የከንፈር ጺምን ብቻ ማሳጠር።
2. ከተመቸ ሙሉ ገላን መታጠብ ሱና ነው

በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች ሳይቀሩ ይታጠባሉ

3. ወንዶች ልብሳቸውን በሙሉ አውልቀው የኢሕራም ልብስ መልበስ ።
4. ሴት ፊቷ ላይ ያለውን ቡርቃ እና ኒቃብ አውልቃ ባዕድ ወንድ ባጋጠማት ጊዜ ከጭንቅላቷ ወርዶ ፊቷን የሚሸፍን ሻሽ መሰል ጨርቅ (ኺማር) ጣል ታደርጋለች።
5. ከትጥበት በኋላ ወንዶች ከኒያ በፊት የኢሕራም ልብሳቸውን ሳይነካ ገላቸውንና ፊታቸውን ቅባትም ሆነ ሽቶ መቀባባት ይችላሉ ።

በኢሕራም ወቅት የሚሰገድ ልዩ የሆነ ሰላት የለም

ሴቶች ከኢሕራም ኒያ በፊት ሽታ የሌለው ቅባት መቀባት ይችላሉ

6. ከኢሕራም ልብስ በኋላ ቀጥታ ወደ ሐጅና ዑምራ ሥራ (ኑሱክ) ነይቶ መግባት ኒያው በቃል ባይሆንም በልብ ካረፈ በቂ ነው የኢሕራሙ ኒያ ከፈርድ ሰላት በኋላ ቢሆን ይመረጣል ያለበለዚያም የውዱእ ሱና ሰላት ሰግዶ ኢሕራም ማድረግ ይቻላል። ሐጅ ወይንም ዑምራ ለሌላ ሰው ማድረግ የፈለገ የሰውዬውን ሥም ጠርቶ (ለበይክ ለእከሌ ማለት ይችላል)

**የተልቢያ አባባል**

(( ለበይክ አላሁመ ለበይክ ለበይክ ላሸሪከለከ ለበይክ ኢነል ሐምደ ወኒዕመተ ለከ ወልሙልክ ላሸሪከለክ))
ትርጉም ፦ አቤት አላህ ሆይ አቤት ፣ አቤት ለአንተ ሸሪክ የለህም ፣ አቤት ምስጋና ፣ ፀጋና ንግሥና ለአንተ ብቻ ናቸው ማሻረክህ የለም።

**የተልቢያው ወቅት**

ለዑምራ ከኢሕራም ኒያ እስከ ጠዋፍ መጀመርያ ድረስ ተልቢያ ሲባል ለሐጅ ከኢሕራም ኒያ እስከ የዒድ ቀን ጠዋት ጀመረቱል ዓቀባህ ላይ ጠጠር እስከሚወረወርበት ሰዓት ድረስ ተልቢያ ይባላል

# የኢሕራም ክልሎች

ረሱል (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ሐጅና ዑምራ ለሚፈልግ ሁሉ ኢሕራም የሚደረግበትን አምስት ክልሎች (ሚቃት) ጠቅሰዋል።

ክልሎቹም

- ዙል ሑለይፋህ
- አል ጁሕፋህ
- ቀርነል መናዚል
- የለምለም
- ዛቱዒርቅ

– ዙል ሑለይፋ ፡- የመዲናና በመዲና በኩል ለሚመጡ ሐጃጆች ኢሕራም የሚያደርጉበት ክልል (ሚቃት) ነው ። በአሁኑ ወቅት አብያር ዓሊ በመባል ይታወቃል።
ከመካ 450 ኪ . ሜ . ይርቃል ።

– አል ጁሕፋ ፡- የሻም ፣ የግብፅ ፣ የሞሮኮና በነሱ በኩል አቋርጠው ለሚመጡ ሐጃጆች ኢሕራም የሚያደርጉበት ክልል ነው ይህ ክልል ለራቢግ ከተማ ስለሚጠጋ በአሁኑ ወቅት ሐጃጆች ከራቢግ ነው ኢሕራም የሚደርጉት።
ከመካ 183 ኪ. ሜ . ይርቃል

– ቀርነል መናዚል ፡- የነጅድና በነሱ በኩል አቋርጠው ለሚመጡ ሐጃጆች ኢሕራም የሚያደርጉበት ክልል ነው ። በአሁኑ ወቅት አስሳይል ከቢር በመባል ይታወቃል።
ከመካ 75 ኪ . ሜ . ይርቃል

– የለምለም ፡- የየመንና በነሱ በኩል አቋርጠው ለሚመጡ ሐጃጆች ኢሕራም የሚያደርጉበት ክልል ነው ሰዎች በአሁኑ ወቅት አስሰዕድያ የሚባለው ቦታ ላይ ነው ኢሕራም የሚያደርጉት።
ከመካ 92 ኪ . ሜ . ይርቃል።

– ዛቱዒርቅ ፡- የኢራቆችና በነሱ በኩል የሚያልፉ ሐጃጆች ኢሕራም የሚያደርጉበት ክልል ነው
ከመካ 94 ኪ . ሜ . ይርቃል ።

ከላይ የተዘረዘሩት የኢሕራም ክልሎች ያለኢሕራም ያቋረጠ የሐጅ መንገደኛ ወደ ክልሉ (ሚቃት) መመለስ ግዴታው ነው ያለበለዚያ እርድ ግዴታ ይሆንበታል

(እርዱም መካ ለሚገኙ ድሃዎች ይከፋፈላል)


## ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት

የሚቃት ክልሎችን ሲያስረዱ ((ሐጅና ዑምራ ለሚፈልግ ለነሱና (ለክልሉ ነዋሪዎች) እንዲሁም ከነሱ ወገን ሳልሆኑ በነሱ በኩል ለሚመጡ )) በማለት አብራርተዋል ።

**— የመካ ከተማ ነዋሪዎች ሐጅ ለማድረግ ከቤታቸው ኢሕራም ሲያደርጉ ዑምራ ለማድረግ ግን ከሐረም ክልል ውጪ ተንዒም ሄደው ኢሕራም ያደርጋሉ ።**

**— መኖሪያቸው ከሐረም ክልል ውጪ ከሚቃት ክልሎች ውስጥ ያሉ ከተሞች እንደ ጅዳ ፣ ሙስተውራ ፣ በድር ፣ በሕራ ፣ ኡምሰሊም ፣ አሽራኢዕ :**

የመሳሰሉት አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ኢሕራም የሚያደርጉት ባሉበት ቦታ ሲሆን ሚቃታቸውም መኖሪያቸው ነው።



## በኢሕራም ወቅት የሚከለከሉ ነገሮች



ከሚቃት ሐጅና ዑምራ ለማድረግ ኢሕራም ከተደረገ በኋላ የሚከለከሉ ነገሮች



- ፀጉርንም ሆነ ጥፍርን መቁረጥ ክልክል ነው ። በአጋጣሚ ፀጉር ቢነቀል ፤ ጥፍር ቢሰበር ወይንም በመርሳትና ባለማወቅ ፀጉርንም ሆነ ጥፍርን መቁረጥ ምንም ችግር የለበትም ።



- ልብስንም ሆነ ሰውነትን ሽቶ መቀባት ክልክል ነው ። ከኢሕራም በፊት የተቀቡት ሽቶ ሽታው በሰውነት ላይ ቢቀር ምንም አይደለም የኢሕራም ልብስ ላይ ግን የሽቶ ሽታ ካለ ማጠብ ያስፈልጋል ።



- ለሙሕሪምም ሆነ ሙሕሪም ላልሆነ ሰው የሐረም ክልል ውስጥ የዱር አራዊትን ማደንም ሆነ ማስበርገግ ክልክል ነው ።



- ለሙሕሪምም ሆነ ሙሕሪም ላልሆነ ሰው የሐረም ክልል ውስጥ ወፍ ዘራሽ የሆኑ ተክሎችን መቁረጥ ክልክል ነው ።



- ለሙሕሪምም ሆነ ሙሕሪም ላልሆነ ሰው የሐረም ክልል ውስጥ የወደቀን እቃ ገንዘብ የመሳሰሉትን ማንሳት ክልክል ነው ። (የወደቀን እቃ ባለቤቱን ለማፈላለግ ማንሳት ይፈቀዳል)

## በኢሕራም ወቅት የሚከለከሉ ነገሮች



- ሙሕሪም የሆነ ሰው ለራሱም ሆነ ለሌላ ሰው ማጨትም ሆነ የጋብቻ ውል መፈፀም ፣ የግብረ - ሥጋ ግንኙነት መፈፀምም ሆነ በስሜት መተሻሸት ክልክል ነው።
ዑስማን (ረዲየሏሁ አንሁ) እንዳወሩት ረሱል (ሰለሳሁ ዓለይሂ ወሰለም)

(ሙሕሪም የሆነ ሰው ማግባት ፣ ማጋባትም ሆነ ማጨት አይፈቀድለትም) ብለዋል ።

ሙስሊም እንደዘገቡት



- በኢሕራም ወቅት ሴት ለእጇ ጓንት ማጥለቅና ፊቷን በኒቃብ ወይንም በቡርቃ መሸፈን ክልክል ነው ።
ነገር ግን ሴት በባዕድ ወንድ መሐል ስትሆን በሒማር (በሻሽ መሰል ብትን ጨርቅ) ፊቷን መሸፈን አለባት ።
ሴት በኢሕራም ወቅትም ሆነ ከኢሕራም ውጭ ፊቷንም ሆነ መላ ሰውነቷን ለባዕድ ወንድ መገለፅ የለባትም ።



- ሙሕሪም የሆነ ወንድ የራስ ቅሉን በኢሕራም ልብስ መሸፈን ፣ ኮፍያ ማድረግ ፣ ራስ ላይ መጠምጠም ክልክል ነው በመርሳት ጭንቅላቱን የተከናነበ እንዳስታወሰ ከንብንቡን ማንሳት አለበት ።



- ሙሕሪም ወንድ ለሙሉም ሆነ ለከፊል ሰውነቱ የተሰፉ ልብሶችን እንደ ሱሪ ፣ ኮት ፣ ቀሚስ ፣ ካልሲ ፣ ሽፍን ጫማ የመሳሰሉትን መልበስ ክልክል ነው ።
(ለኢሕራም የሚሆን ብትን ጨርቅ ማግኘት ካልተቻለ የተሰፉ ልብሶችን መልበስ ፣ ነጠላ ጫማም ካልተገኘ ሽፍን ጫማ መጫማት ይቻላል)



# ለሙሕሪም የሚፈቀዱ ነገሮች












- ሰዓት
- የጆሮ ማዳመጫ
- ቀለበት
- ነጠላጫማ
- መነፅር
- ቀበቶ
- በጃንጥላ መጠለል
- መኪና ውስጥ መጠለል
- በራስ ላይ ዕቃ መሸከም

## ሌሎች የሚፈቀዱ

- ቁስልን ማሸግ የኢሕራም ልብስ ማጠብና መቀየር
- የራስ ፀጉርንና ገላን መታጠብ
- ሙሕሪም ሳያውቅ ፀጉር ቢነቀልበት ምንም አይደለም
- ሕጉን ባለማወቅም ሆነ በመርሳት የራስ ቅልን የሸፈነ ወንድ እንዳወቀ ወይንም እንዳስታወሰ ሽፋኑን ማንሳት ብቻ በቂ ነው ።

# የሐጅና ዑምራ አደራረግ አይነቶች

### ሦስቱ የሐጅና ዑምራ አፈፃፀም

ሐጅ ለማድረግ የፈለገ ከሦስቱ የሐጅ አደራረግ አይነቶች አንዱን መምረጥ ይቻላል ::

**1 አተመቱዕ** — ዑምራ — ሐጅ — ዕርድ ግዴታ

ተመቱዕ ማለት በሐጅ ወራቶች ውስጥ ለዑምራ ነይቶ ኢሕራም ማድረግ ሲሆን የሐጅ ወራቶች ማለት ሸዋል፣ ዙልቂዕዳ እና በዙልሒጃ አስር ቀናች ናቸው ። ከኢሕራም ኒያ በኋላ (ለበይክ ዑምራ ሙተመቲዓን ቢሃ ኢለል ሐጅ) ይባላል ። ትርጉሙም ዑምራ አድርጌ እስከ ሐጅ ድረስ በኢሕራም ወቅት የተከለከሉትን ነገሮች ተጠቅሜ ሐጅ ሲደርስ በድጋሚ ኢሕራም ሳደርግ) ማለት ነው ።በመቀጠል ለዑምራ ጠዋፍና ሰዕይ ካደረጉ በኋላ ፀጉርን አሳጥሮ ኢሕራም መፍታት።ዙልሒጃ ስምንት ሲደርስ ካሉበት ቦታ ኢሕራም አድርጎ ወደ ሚና በመሄድ የሐጁን ሥነ ሥርዓት ማካሄድ በዚህን ግዜ በግ ማረድ ግዴታ ይሆናል ሌላው አማራጭ አንድ በሬ ወይንም ግመል ለሰባት ሰው ሆኖ ማረድ ይቻላል ። ማረድ ያልቻለ አሥር ቀን መፆም አሰበት ፆሙም ሦስት ቀን ሐጅ ላይ ሆኖ ሰባቱን ሃገሩ ሲመለስ ይፆመዋል።

**2 ቂራን** — ዑምራና — ሐጅ — ማረድ ግዴታ

ቂራን ማለት ኢሕራም አድርጎ ሐጅና ዑምራን አንድ ላይ ማድረግ ማለት ነው ። ኒያውም (ለበይክ ዑምረተን ወሐጀን) ማለት ሲሆን ። መካ እንደደረሱ ጠዋፈል ቁዱምና ሰዕይ ማድረግ ሰዕዩ ለዑምራም ለሐጅም ይሆናል ኢሕራሙንም ሳይፈታ እስከ ዙልሒጃ ስምንት ቆይቶ ዙልሒጃ ስምንት የሐጅ ሥራን ለማከናወን ወደ ሚና መጓዝ ሚና ዓረፋና ሙዝደሊፋ የሚሰሩትን ሥራዎችን ካጠናቀቁ በኋላ ለጠዋፈል ኢፋዷ ወደ መካ ሲመለሱ መጀመርያ ለዑምራና ለሐጅ ሰዕይ ስለተደረገ ሌላ ሰዕይ ማድረግ አይገባም በመቀጠል በግ ማረድ ግዴታ ሲሆን ማረድ ያልቻለ አሥር ቀን መፆም አሰበት ፆሙም ሦስት ቀን ሐጅ ላይ ሆኖ ሰባቱን ሃገሩ ሲመለስ ይፆመዋል።

**3 ኢፍራድ** — ሐጅ ብቻ — ማረድ ግዴታ አይሆንም

ኢፍራድ ማለት ለሐጅ ብቻ ኢሕራም አድርጎ ሚቃት ሲደርስ ለበይክ ሐጀን ይላል መካ እንደደረሰ የመግቢያ ጠዋፍ (ጠዋፈል ቁዱም) እና የሐጅን ሰዕይ ያደርጋል የሐጅን ሰዕይ ከሚና መልስ ማድረግ ይቻላል ።

ከብት ሳልነዳ የተመረጠው የሐጅ አደራረግ (ኑሱክ) ተመቱዕ ነው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሰሐባዎቻቸው የመረጡት የሐጅ አደራረግ ተመቱዕ ነበር።

# ስለሐጅና ዑምራ ጠቅላላ ዕውቀት

| ሙፍሪድ ሐጅ ብቻ | ቃሪን ሐጅና ዕምራ እንድላይ | ተመቱዕ ዑምራ አድርጎ ሐጅ ድረስ መፍታት |
|---|---|---|
| ሁሉም ኢሕራም ከሚቃት ያደርጋሉ | | |
| 1 የመግቢያ ጠዋፍ | የመግቢያ ጠዋፍ | የዑምራ ጠዋፍ |
| 2 ለሐጅ ሰዕይ | ለሐጅና ዑምራ ሰዕይ | ለዑምራ ሰዕይ |
| | | የራስ ፀጉርን ማሳጠር ወይንም መላጨት |
| እስከ ዙልሒጃ ስምንት በኢሕራሙ ይቆያል በኢሕራም ወቅት ክልክሎችን ሁሉ ይከለከላል | እስከ ዙልሒጃ ስምንት በኢሕራሙ ይቆያል በኢሕራም ወቅት ክልክሎችን ሁሉ ይከለከላል | ኢሕራሙን ፈትቶ ክልክሎች ሁሉ ግብረ -- ሥጋ ጨምሮ ይፈቀዱል |
| | | የውመል ተርዊያ ለሐጅ ዙልሒጃ ስምንት ኢህራም ያደርጋል |

1 ለሙፍሪድ የመግቢያ ጠዋፍ ሱና ስለሆነ ቢተወውም ምንም አይደለም

2 ለሙፍሪድ የመግቢያ ጠዋፍ ብቻ አድርጎ ወደ ሚና ከሄደ ሲመለስ ከጠዋፈል ኢፋዳ በኋላ ሰዕይ ማድረግ ይገባዋል ::

ክፉና ደጉን መለየት የማይችሉ ሕፃናት ሐጅ ሲያደርጉ ኒያውን የሚያደርጉላቸው ወላጆቻቸው ሲሆኑ አዋቂ ሙሕሪም የተከለከለውን ሁሉ ይከለከላሉ በተለይ በጠዋፍ ወቅት ጡሓራ መሆን አለባቸው ጠዋፍ እንደ ሰላት ስለሆነ ጡሓራና ውዱዕ ግዴታ ነው። ክፉና ደጉን መለየት የሚችሉ ነገር ግን ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሕፃናት በወላጆቻቸው ፈቃድ ሐጅ ሲያደርጉ ሚቃት ላይ እንደ አዋቂዎች መታጠብ መበጃጀትና የመሳሰሉትን ማድረግ አለባቸው።

# የዑምራ አደራረግ



قال ﷺ

العمرة إلى العمرة
كفارة لما بينهما
والحج المبرور
ليس له جزاء إلا الجنة
متفق عليه

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ከዑምራ እስከ ዑምራ ያለው ጊዜ የወንጀል ማካካሻ ነው ሐጅል መብሩር (ተቀባይነት ያለው ሐጅ) ምንዳው ጀነት ነው) ብለዋል።

# የዑምራ ጠዋፍ

## ዑምራ ለማድረግ መከተል ሙከረማ እንደደረሱ

ወዲያው ታጥቦ ወደ ጥንታዊው የአላህ ቤት መስጂደል ሐረም መሄዱ ይወደዳል መታጠቡ ግዴታ አይደለም ።

– መስጂደል ሐረም ሲገባ ቀኝ እግርን በማስቀደም ፡፡-
እንደሚከተለው ይባላል
( አዑዙቢላሂል ዓዚም ወወጀሁሁል ከሪም
ወሱልጣኑሁል ቀዲም ሚነሸይጧኒረጂም
አላሁመ እፍታሕ ሊ አብዋበ ረሕሙቲክ)

ትርጉም ( በሃያሉ ጌታ የተከበረ ፊትና የነባር ስልጣን ባለቤት በሆነው አላህ
ከእርጉሙ ሸይጧን ከፋት እጠበቃለሁ )
« አላህ ሆይ የእዝነት በርህን ክፈትልኝ »

ይህ ዱዓ ማንኛውም መስጊድ ሲገባ ይደረጋል

## የዑምራ ሥራ ለመጀመር

ወደ ተከበርው ካዕባ በሙሄድ ጠዋፍ ማድረግ ለወንድ በጠዋፈል ቁዱም ግዜ ብቻ የቀኝ ትከሻን ግልፅ ማድረግ ሱና ነው ።

## ሌላው በዑምራ ወቅት

ጠዋፍ ሲደረግ ካዕባን ሰባት ግዜ መዞር ሲሆን ዙሩ የሚጀምረው ከሐጀረል አስወድ ነው ።
– በጠዋፍ ግዜ የተመቸው ሐጀረል አስወድን መሳም ይችላል ካልተመቸው በርቀት አላሁ አክበር በማለት እጁን እንስቶ ያመለክታል በተረፈ ሰው በበዛበት ግዜ ሐጀረል አስወድን ለመሳም ብሎ ከሙስሊሞች ጋር መጋፋት መሰዳደብና መደባደብ ትልቅ ስህተት ነው ።



ሌሎችን ሰዎች መጋፋትም ሆነ ማሰቃየት የተከለከለ ነው

# የዑመራ ጠዋፍ

### ጠዋፉን በመቀጠል

– በካዕባ ዙርያ ጠዋፍ በሚደረግበት ግዜ አላህን እያወሱ እስቲግፋርና የፈለጉትን ዐይነት ዱዓ እያደረጉ ቁርአን እየቀሩ ሰባት ግዜ ይዞራል ።

– በተወሰኑ ዱዓዎች ብቻ ድምፅን ከፍ አድርጎ ዚክር ማለት ጠዋፍ የሚያደርጉ ሰዎችን መረበሽ ስለሆነ ስህተት ነው ።

### በጠዋፍ ግዜ ሩክነል የማኒ ሲደረስ

ሩክነል የማኒ የሚባለው የካዕባው ማዕዘን ሲደረስ ከተመቸ በእጅ እመላክቶ ሰላም ማለቱ ብቻ በቂ ነው ። ሩክነል የማኒን መሳምና መደባበስ የረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም ) ሱና አይደለም፡ ካልተመቸ ሰላም ማለቱ ቢቀርም ምንም አይደለም፡፡

ዋና ሱናው በጠዋፍ ግዜ ሩክነል የማኒና ሐጀረር አስወድ መካከል ሲደረስ ።

رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِى ٱلْءَاخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ

سورة البقرة

(( ረበና አቲና ፊዱንያ ሐሰኑተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና አዛበናር )) ይባላል


### በዚሀ መልኩ ዑምራው ይካሄዳል

– ከላይ በተብራራው መሠረት ከሐጀረል አስወድ ተጀምሮ ዞሮ ሐጀረል አስወድ ሲደረስ አንድ ዙር እየተባለ ሰባት ዙር ይዞራል ።

– በጠዋፈል ቁዱም ጊዜ ብቻ ለወንድ የመጀመሪያ ሦስት ዙሮችን ፈጠን ፈጠን እያሉ መጠወፍ ሱና ነው ።

# ሐጀረል አስወድ






ጠዋፍ ሚጀመረው ከሃጀረል አስወድ ሲሆን
የሚጠናቀቀውም ሐጀረል አስወድ ላይ ነው

## በጠዋፍ ወቅት ስህተቶች

ካዕባው አጠገብ ከሐጀረል አስወድ በግራ በኩል በአጭር የተገነባ ክልል የካዕባው ክልል በመሆኑ በጠዋፍ ጊዜ አንድ ላይ መዞር አለበት።

ሒጅር ማለት የካዕባው ክልል ነው

የካዕባን ማዕዘኖች በጠቅላላ ሰላም ማለት ግድግዳውን ፣ የካዕባን ጨርቅ ፣ መቃመ ኢብራሂምን ፣ መደባበስና መሳም ባጠቃላይ በሸሪዓው የማይታወቅም ፈጠራ ነው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሲያደርጉት አልታየም ።
በጠዋፍ ግዜ ሴቶችና ወንዶች በተሰይ ሐጀረል አስወድና

መቃመ ኢብራሂም አካባቢ መገፋፋትና መተሻሸት አግባብ ስላልሆነ ከእንደዚህ አይነት የግፊያ ቦታ ሰውን ላለመግፋት መጠንቀቅ ያስፈልጋል ።

ጠዋፍ እንደተጠናቀቀ የሚሰሩ ስራዎች

1 ኛ - ወንዶች ግልፅ ያደረጉትን የቀኝ እጅ መሸፈን።
2 ኛ - ከመቃመ ኢብራሂም ጀርባ ረከዓተይን ሰላት መስገድ ካልተመቸ ሐረም ውስጥ የተገኘው ቦታ መስገድ ይቻላል ።ይህም ሱና ሙአከዳ ነው ረከዐተይን ሲሰገድ በመጀመርያው ረከዓ ከፋቲሐ በኋላ

ሱረቱል ካፊሩን سُورَةُ الْكَافِرُونَ

ሲቀራ ከሁለተኛው ረከዓ ፋቲሐ በኋላ

ሱረቱል ኢኽላስ ይቀራል። سُورَةُ الإِخْلَاصِ

ከነዚህ ሌላ ምዕራፍ ቢቀራ ምንም አይደለም ።

# የዑምራ ሰዕይ (ሰፋ መርዋ)

**ጠዋፍ ከተጠናቀቀ በኋላ**

- ሰዕይ ወደሚደረግበት ቦታ ሰባት ግዜ ለመመላለስ ወደ ሰፋ ኮረብታ ይኬዳል ኮረብታው ላይ እንደደረሱ አላህ እንደጀመረው እንዲህ በማለት ይጀመራል ፡፡ ﴿ إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلْمَرْوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِ

((ኢነሰፋ ወል መርወተ ሚን ሸዓኢሪላህ ))

**የሰፋ ኮረብታ ላይ ወጥቶ**

ፊትን ወደ ካዕባ በማዞር ሃያሉን አላህ እያመሰገኑ ሦስት ግዜ አላሁ አክበር በማለት እጆችን ዘርግቶ ዱዓ እያደረጉ እንዲህ ይባላል

(( ላኢላሃ ኢለሏህ ዋሕደሁ ላሸሪከለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሽይኢን ቀዲር))

**- ትርጉሙ**

(( ከአላህ በስተቀር በሐቅ የሚያመልኩት ጌታ የለም አንድ ነው አጋርም የለውም -- ግዛት ሁሉ የሱ ነው ምስጋናም ለሱ ነው እሱም በሁሉ ነገር ላይ የችሎታ ባለቤት ነው ))

ይህ ዚክር ሦስት ግዜ ይደጋገማል

- በሰፋ ላይ የፈለጉትን አይነት ዱዓ አስረዝሞም ሆነ አሳጥሮ ማድረግ

- በዱዓ ጊዜ በስተቀር በተክቢራ ጊዜ እጆችን ዘርግቶ ወደ ካዕባ ማመላከት አግባብ አይደለም፡- ብዙ ሐጃጆችና ዑምራ የሚያደርጉ ሰዎች ሰፋ ወይንም መርዋ ኮረብታ ላይ ሆነው እጃቸውን አንስተው ወደ ካዕባው ሰላም ይላሉ ይህ መታረም ያለበት ስህተት ነው ፡፡

**ከሰፋ ኮረብታ በመውረድ**

ወደ መርዋ ኮረብታ እየተጓዙ ለራስ ለቤተሰብና ለሙስሊሞች የፈለጉትን ዱዓ ማድረግ፡፡

- በሰፋ መርዋ መካከል ካሉት የመጀመርያው አረንጓዴ ምልክት ላይ እንደደረሱ ወንዶች ብቻ ያረማመዳቸውን ፍጥነት ይጨምራሉ

- የሁለተኛው አረንጓዴ ምልክት ሲደርሱ ፍጥነቱን ቀንሰው በዝግታ ይጓዛሉ፡፡

# መርዋ

## የመርዋ ኮረብታ ሲደረስ

- የመርዋ ኮረብታ ሲደረስ ፊትን ወደ ካዕባ በማዞር ልክ ሰፋ ኮረብታ ላይ የተባለውን ዚክር በመድገም የፈለጉትን ዱዓ በማድረግ ከመረዋ ወደ ሰፋ መጊዝ በሁለቱ አረንጓዴ ምልክቶች መሃል ሲደረስ እንደ መጀመርያው ወንዶች ያረማመዳቸውን ፍጥነት ይጨምራሉ ሰፋ ላይ ሲደረስ ሁለት ምልልስ አለቀ ማለት ነው በዚህ መልኩ ሰባት ግዜ በመመላለስ ሰፋ ላይ የተጀመረው ምልልስ (ሰዕይ) መርዋ ላይ ይጠናቀቃል ::

- ሰዕይ ሲደረግ ሰባቱን ምልልስ ሳይጨርስ የደከመው ወይንም የታመመ አረፍ ብሎ መቀጠል ወይንም በጋሪ ላይ ቁጭ ብሎ እየተገፋ ምልልሱን መጨረስ ይቻላል ::



## በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ላሉ ሴቶች የሚፈቀደው

- ጠዋፍ ማድረግ አይችሉም ሰፋ መርዋ ምልልስ ግን ከሐረም መስጊድ ውጪ ስለሆነ ይፈቀዳል



## ግልፅ ስህተቶች



## በአረንጓዴዎቹ ምልክቶች መሐከል ሴቶች መፍጠን የለባቸውም


- ሰዕዩን ከጨረሱ በኋላ ወንዶች ፀጉራቸውን በሙሉ መላጨት ወይንም በሙሉ ማሳጠር አለባቸው ::
- ሴቶች ከሙሉ ፀጉራቸው ጫፍ  የጣት አንጓ ያህል መቁረጥ አለባቸው::




## ከላይ በተብራራው መልኩ የዑምራ ሥራ ሲጠናቀቅ

በመጨረሻ በኢህራም ወቅት የተከለከሉ ነገሮች በሙሉ ይፈቀዳሉ

## ሰዕይ ከሰፋ ተጀምሮ መርዋ ላይ ይጠናቀቃል





# የሐጅ አፈፃፀም

قال ﷺ

من حج فلم يرفث ولم يفسق

رجع من ذنوبه

كيوم ولدته أمه

حديث صحيح

...ል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)
...ዝ - ሥጋ ሳይፈጽምና ሳይጨቃጨቅ ሐጅ ያደረገ እናቱ
...ወለደችው ቀን ከወንጀል ነፃ ሆኖ ይመለሳል ) ብለዋል። ሐዲስ

# የዙልሒጃ ስምንተኛው ቀን

## የውመ ተርዊያ

– ዙልሂጃ ስምንት የሐጅ ሥራዎች ይጀመራሉ

**ቀኑም የውመል ተርውያ ይባላል**

በዚህ ቀን ተመቱዕ የሆነ ሰው ባለበት ወይንም በሰፈረበት ቦታ ኢሕራም ያደርጋል:: ለሐጅ ኢሕራም ሲያደርግ ልክ ለዑምራ ኢሕራም ሲያደርግ ታጥቦ ፣ ተበጃጅቶ ፣ ሰግዶ እንዳደረገው ያደርጋል ::

**ከዙሁር በፊት**



– ቃሪንና እና ሙፍሪድ የሆኑ በኢህራማቸው ስለቆዩ ካሉበት ቦታ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይነሳሉ::

**ዙሑር ዓሥር መቅሪብና ዒሻ መስገድ**

ተመቱዕ ቃሪንና ሙፍሪድ ሁሉም በአንድ ላይ ከዙሁር በፊት ወደ ሚና መንቀሳቀስ ይጀምራሉ :: ሚናም እንደደረሱ የዙሑር የአሥር የመግሪብ እና የኢሻ ሰላቶች ሁሉንም በወቅታቸው ሳያቆራኙ በተናጠል ባለአራት ረከዓት ሰላቶችን ብቻ ወደ ሁለት በማሳጠር ይሰግዳሉ ::



– ለዙልሒጃ ዘጠነኛው ቀን አጥቢያ ሌሊቱን እዛው ሚና ይታደራል::

– ከዙልሂጃ ስምንተኛው ቀን በተለያየ ምክንያት ሚና የገባ ዙልሒጃ ስምንት ጠዋት ላይ ኢሕራም ያደርጋል ::

**ሚና ማደር**

– ዙልሒጃ ስምንት ሚና ማደር ከሐጅ ሱናዎች አንዱ ነው ::

– ዙልሒጃ ዘጠኝ ሚና ላይ የፈጅር ሰላት ከተሰገደ በኋላ ፀሐይ እንደወጣች ሳይቻኮሉ በእርጋታ ወደ አረፋ ምድር ጉዞ ይደረጋል ::

– በጉዞ ወቅት እየደጋገሙ ተልቢያ በማድረግ አላህን ማውሳት ቁርአን መቅራትና የዓለማቱን ጌታ አላህን ማመስገን ይወደዳል ::

# ዙልሒጃ ዘጠነኛው ቀን

## የዓረፋ ቀን

— ፀሐይ ከወጣችበት ወቅት ጀምሮ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ዓረፋ ላይ መቆም ከሐጅ መሠረቶች አንዱ ነው ያለሱም ሐጅ አይሟላም

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)

**ሐጅ ማለት ዐረፋ ነው**

ብለዋል

አቡ ዳውድና ተርሚዚ

ፀሐይ ስትወጣ ጀምሮ



## የዓረፋ ቀን

— ፀሐይ ከወጣችባቸው ቀኖች ሁሉ የተመረጠው ነው
— በዚህ ቀን ሐጃጆች በሙሉ ወደ ዓረፋ ይጎርፋሉ
— በዚህ በተከበረው ቀን ሐጃጆች ፀሐይ ወጥታ እስክትጠልቅ ድረስ ዓረፋ ምድር ይቆማሉ
— አላህም በሐጃጆቹ በመደሰት የባሮቹን ዝና ለመላኢኮች ያንፀባርቃል

ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ



ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት (ከቀኖች ሁሉ እንደ ዓረፋ ቀን አላህ ባሮቹን ከእሳት ነፃ የሚያወጣበት ቀን የለም በዚህ ቀን ሃያሉ አላህ (ወደ ምድር) ወረድ በማለት የሐጃጆቹን ዝና ለመላኢኮች ያንፀባርቃል

ምን ይፈልጋሉ እነዚህ ?? ይላል

አላህን ፀጋውንና ደግነቱን እንለምነዋለን

# የዙልሒጃ ዘጠነኛ ቀን

## የዓረፋ ቀን

-ዐረፋ



-የዙሁርና የዓስር ሰላት አንድ ላይ መስገድ



-ፀሐይ እንደጠለቀች

ሙዝደሊፋ መጊዝ

ከዐረፋ ቀን ሱናዎች:-

– ከተመቸ ነሚራ መስጊድ ውስጥ መግባት

– ዋናው የዓረፋ ክልል መግባትን ማረጋገጥ ። ዓረፋ ምድር ላይ የዓረፋን ክልልሎች የሚያመላክቱ ብዙ ምልክቶችና ሰሌዳዎች ይኖራሉ ፡ ይህ የዓረፋ ክልል በጠቅላላው መቆምያ (መውቁፍ) ነው በዚህ በተከበረው ቀን ሐጃጆች በተልብያ ፣ በዚክር ፣ እስቲግፋር በማብዛት አላህን እያወደሱና እያመሰገኑ ፈጣሪያቸውን ፈርተውና ተናንሰው ለራሳቸው ፣ ለቤተሰባቸው ለልጆቻቸውና ለወንድሞቻቸው ለሙስሊሞች በጠቅላላ ዱዓ በማድረግ ጊዜያቸውን ይጠቀማሉ ።

– የዙሁር ሰላት ሲደርስ ኢማሙ የሚያደርገውን ኹጥባ ያዳምጣሉ በመቀጠል ኢማሙ ሐጃጆችን የዙሑርንና የዓስርን ሰላት አሳጥሮ በአንድ አዛንና በሁለት ኢቃም ያሰግዳቸዋል።

– ይህም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳደረጉት ከዙሁርና ከዓስር ሰላቶች በፊትም ሆነ በኋላ ወይንም በመካከል ምንም ሰላት አልሰገዱም።

--ሐጃጆች በዚህ በተከበረ ቀን ምንዳቸውን ከሚያበላሹ ወይንም ከሚያሳንሱ ስሕተቶችና ወንጀሎች መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል ።



## ግልፅ ስህተቶች

የዓረፋ ቀን ሐጃጆች ሊጠነቀቁባቸው የሚገቡ ብዙ ስህተቶች ይታያሉ ከነሱም በጥቂቱ:-

- አንዳንድ ሐጃጆች ከዓረፋ ክልል ውጪ በመስፈር ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ቆይተው የዓረፋ ክልል ሳይገቡ ቀጥታ ወደ ሙዝደሊፋ ይመለሳሉ እንደነዚህ አይነት ሐጃጆች ሐጃቸው ተበላሸ ማለት ነው ፡፡

- ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የዓረፋን ክልል ለቆ መውጣት ክልክል ነው የረሱልንም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሱና መቃረን ነው ፡፡

  ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የዓረፋን ክልል ለቆ የወጣ ማረድ (ደም) ግዴታ ይሆንበታል፡፡

- የዓረፋ ተራራ ጫፍ ላይ በመውጣት ግፍያና ትርምስ መፍጠር ስላት መስገድና ድንጋይ መደባበስ በኢስላም የማይታወቅ ፈጠራ (ቢድዓ) ከመሆኑም አልፎ ለአደጋ መጋለጥ ስለሆነ መቆጠብ ያስፈልጋል ፡፡

- ሌላው ፊትን ወደ ዓረፋ ተራራ አዙሮ መስገድ ትልቅ ስህተት ነው ፡፡

✓ በዱዓ ጊዜ ፊትን ወደ ቂብላ ማዞር ትክክለኛው ሱና ነው ፡፡



# ሙዝደሊፋ

## ዙልሒጃ ዘጠኝ ፀሐይ እንደጠለቀች

በአላህ በረካ ሐጃጆች ወደ መሽዓረል ሐራም ሙዝደሊፋ ይጓዛሉ ፡ ሙዝደሊፋ እንደደረሱ የመግሪብንና የኢሻን ሰላት አሳጥረው አንድ ላይ በማከታተል በአንድ አዛንና በሁለት ኢቃም ይሰግዳሉ ሌሊቱንም እዛው አድረው ዓረፋ ለመቆም ያበቃቸውን አላህ እያመሰገኑና እያወደሱ ለበይክ አላሁመ ለበይክ (ተልብያ) ይላሉ ፡፡

ሙዝደሊፋ በሚታደርበት ሌሊት የሚከሰቱ ስሕተቶች

- መግሪብና የኢሻን ሰላት ሳይሰግዱ ጠጠር ለመልቀም መቻኮል
- የሚለቀመው ጠጠር የግድ ከሙዝደሊፋ ነው ብሎ ማመን ስህተት ነው ከሚናም ቢሆን መልቀም ይቻላል ፡፡
- የለቀሙትን ጠጠር ማጠብ ስህተት ሲሆን ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አላደረጉትም፡፡

ሐጃጆች ሙዝደሊፋ ላይ የፈጅር ሰላት ከሰገዱ በኋላ መሽዓረል ሐረም ተራራ እንደደረሱ ፊታቸውን ወደ ቂብላ አዙረው የፈለጉትን ዱዓ ማብዛት ይወደዳል፡፡

ወደ ሚና በሚጓዙበት ጊዜ ጀምረቱል ኩብራ ላይ ለመወርወር ሰባት ጠጠር ይለቀማል የተቀረውን ሚናም ላይ መልቀም ይቻላል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ሱናው ሐጃጆች ለሊቱን የፈጅር ሰላት እስኪሰግዱ ድረስ ሙዝደሊፋ ያድራሉ፡፡

ነገር ግን ለደካማ ፣ ለሴቶች ፣ ለህፃናት ፣ ለህመምተኞችና ለጠባቂዎቻቸው ዕኩለ ሌሊት ላይ ሙዝደሊፋን ለቀው መውጣትና ወደ ሚና መጓዝ ይፈቀድላቸዋል ፡፡

በመቀጠል በአላህ በረካና እርዳታ ተልቢያ እያሉ አላህን እያመሰገኑና እያወደሱ ወደ ሚና ይጓዛሉ ፡፡

ተልቢያ ፡ - ለበይክ አላሁመ ለበይክ -ለበይክ ላሸሪ ከለክ ለበይክ ኢነል ሐምደ ወኒዕመተ - ለከወልሙልክ ላሸሪከለክ

ፀሐይ እንደጠለቀች



ጉዞ ወደ ሙዝደሊፋ



የመግሪብና የኢሻን ሰላት አሳጥሮ በአንድ ላይ መስገድ

ሙዝደሊፋ ማደር

ፈጅርን መስገድ

ዚክርና ዱዓ ማድረግ

ጠጠር መልቀም



ወደ ሚና መጓዝ

# ሚና እንደደረሱ

## ለመካ ቅርብ ወደሆነው ጀመረቱል ኩብራ መሄድ

ልክ ጀመረቱል ኩብራ እንደደረሱ ተልቢያ ማለት በማቆም የሚከተሉትን ማከናወን፡፡

1



ጀምረቱል ኩብራ ላይ እያንዳንዱን ጠጠር በየተራ አላሁ አክበር እያሉ ሰባት ጊዜ መወርወር፡፡



2



የመስዋዕት እርድ ያቀረበ ከብቱን አርዶ ለራሱ በልቶለት ለድሆች ማከፋፈል፡፡



3



በመቀጠል ወንዶች ፀጉራቸውን በሙሉ ይላጩታል ወይንም ያሳጥሩታል መላጩቱ የተሻለ ነው፡፡ ሴቶች ከሙሉ ፀጉራቸው ጫፍ ላይ የአንድ ጣት አንጓ ርዝመት ያህል ያሳጥራሉ፡፡



ከላይ የተዘረዘረው ቅደም ተከተል የተሻለ ሲሆን ማዛባቱ ምንም ችግር አይፈጥርም ፡፡

# ዙልሒጃ አሥር

ዙልሂጃ አሥር የዒድ አል አዷሐ ቀን የውመ ነሕር (የእርድ ቀን) ይባላል

ከምድር ዙርያ የተሰባሰቡ ሙስሊሞች (ሐጃጆች) በተለየ መልኩ የዒድ አል አድሐን ቀን በከፍተኛ ደስታ በማክበር ለሐጅ ያበቃቸውን አላህ እያመሰገኑ ወደ አላህ ለመቃረብ ያዘጋጁትን ከብት በማረድና ጀመረቱል ኩብራ (ዑቅባ) ላይ ጠጠር ከወረወሩ በኋላ በሚከተሰው መልኩ አላህን በማተለቅ ተክቢራ ይላሉ :-

አላሁ አክበር አላሁ አክበር አላሁ አክበር
ላኢላሃ ኢለላህ አላሁ አክበር ወሊላሂል ሐምድ

ጀመራት ላይ በሚወረወርበት ጊዜ የአንዳንድ ሐጃጆች ስህተት:-

- እንዳንድ ሐጃጆች ጠጠሩን ሸይጣን ላይ የሚወረውሩ አስመስለው ቁጭት እልህና ስድብ ይታይባቸዋል ይህ ሁሉ ስህተት ነው ጀመራት ላይ መወርወር የታዘዘው የአላህን ትዕዛዝ ለማክበር ብቻ ነው ::
- ጀመራት ላይ ትልልቅ ድንጋይ ፣ ጫማና ፣ እንጨት የመሳሰሉትን መወርወር ትልቅ ስህተትና ረሱል (ሰለላሁዓለይሂ ወሰለም) የከለከሉት በዲን ላይ ድንበር ማለፍ ነው::
- ጀመራት አካባቢ ግፍያ መፍጠርና መረጋገጥ ትልቅ ስህተት ነው እያንዳንዱ ሐጅ ለወንድሙ ማዘንና መደጋገፍ ግዴታው ነው:
- ጠጠሮችም ትክክለኛው ቦታ ጉድጓድ ውስጥ መግባት አለባቸው ቋሚ ግድግዳውን ቢመቱትም ባይመቱትም ምንም ለውጥ የለውም::
- ሰባቱንም ጠጠር በአንድ ላይ መወርወር ትክክል አይደለም ሰባቱን ጠጠር አንድ ላይ መወርወር እንደ አንድ ጠጠር ነው የሚቆጠረው : ትክክለኛው አወራወር እያንዳንዱን ጠጠር ለየብቻ ተክቢራ እያሰሙ መወርወር አለበት ::

– ጀምረቱል ዓቀባ ላይ ጠጠር ተወርውሮ ፀጉርን ከተላጩ ወይንም ካሳጠሩ በኋላ የመጀመርያው ተሐሉል ስለተጠናቀቀ የኢሕራም ልብስ አውልቆ ወደ መደበኛ ልብስ በመመለስ

ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በስተቀር በኢሕራም ወቅት የተከለከሉ ነገሮች በሙሉ ይፈቀዳሉ

ወደ ጀመራት መሔድ



ተልቢያ ማቆም

ጀመረቱል ዓቀባ ላይ ጠጠር መወርወር

ለዒድ ተክቢራ ማለት



መስዋዕት (ሐድይ) ማረድ



ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር

# የጀመራት አወራወር

1 **የዒድ ቀን ጠዋት ከሙዝደሊፋ ወደ ሚና ከተመለሱ በኋላ የሚከተሉትን ማድረግ**



ጀምረቱል ዐቀባ ላይ ብቻ ሰባት ጠጠር መወርወር በእያንዳንዱ ውርወራ ተክቢራ ማሰማት

ጀምረቱል ዓቀባ




2 **ሦስት ተከታታይ ቀኖች (አያመል ተሽሪቅ)**

ሦስቱም ጀመራት ላይ በየቀኑ መወርወር ::አወራወሩ መጀመርያ ትንሹ ጀመራት (ሱግራ) ከዛም መሐከለኛው ጀመራት (ውስጧ) በመጨረሻ ትልቁ ጀምረቱል (ዓቀባ) ላይ ይወረወራል::

ሁሉም ጀመራት ላይ ሰባት ጠጠር ከተክቢራ ጋር መወርወር



# ጠዋፈል ኢፋዳ

ጠዋፈል ኢፋዳ ካልተደረገ ሐጁ ሙሉ አይሆንም ምክንቱም የሐጅ መሠረት ነውና።

– የኢድ ቀን ጀምረቱል ዓቀባ ላይ ጠጠር ከተወረወረ በኋላ ጠዋፈል ኢፋዳ ለማድረግ ወደ መካ ሐረም መስጊድ በመሄድ በካዕባ ዙርያ ሰባት ዙር ጠዋፈል ኢፋዳ ይደረጋል ።
በዚህ ቀን ሙተመቲዕ የሆኑ የሐጅ መሠረት ሰዕይ ያደርገሉ ። ኢፍራድ ወይንም ቃሪን የነዩቱ መጀመርያ ከጠዋፈል ቁዱም ጋር የሐጅ ሰዕይ ያላደረጉ ከሆን በዚህ ቀን ያደርጋሉ።-
– ጠዋፈል ኢፋዳ የሚና ሥራ አልቆ ወደ መካ ሲመለሱ ማድረግ ይቻላል።



የዒድ ቀን ጠዋፈል ኢፋዳ ከተደረገ በኋላ በኢሕራም ወቅት ክልክሎች በጠቅላላ ይፈቀዳሉ ...... ግብረ ሥጋንም ይጨምራል

# አያመል ተሽሪቅ

**አያመል ተሽሪቅ ዙልሒጃ አሥራ አንድ ይጀምራል**

- የዒድ ቀን ጠዋፈል ኢፋዳ ከተደረገ በኋላ ሦስቱን ቀን (አያመል ተሽሪቅ) ሚና ለማደር ሐጃጆች ወደ ሚና ይመለሳሉ ።
- የፈለገ ወይንም የቸኮለ አያመ ተሽሪቅ ሁለት ቀን ብቻ ማደር ይቻላል ለዚሁም አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል ፦

۞ وَاذْكُرُوا اللَّهَ فِي أَيَّامٍ مَّعْدُودَاتٍ ۚ فَمَن تَعَجَّلَ فِي يَوْمَيْنِ فَلَا إِثْمَ عَلَيْهِ وَمَن تَأَخَّرَ فَلَا إِثْمَ عَلَيْهِ ۚ لِمَنِ اتَّقَىٰ ۗ وَاتَّقُوا اللَّهَ وَاعْلَمُوا أَنَّكُمْ إِلَيْهِ تُحْشَرُونَ ﴿٢٠٣﴾

ትርጉም ((በተቆጠሩ ቀኖችም ውስጥ (በሚና ጠጠሮችን ስትወረውሩ) አላህን አውሱ በሁለት ቀኖችም ውስጥ (ለመሄድ) የተቻኮለ ሰው በርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም የቆየም ሰው በሱ ላይ ኃጢአት የለበትም (ይህም) አላህን ለፈራ ሰው ነው አላህን ፍሩ እናንተ ወደርሱ የምትሰበሰቡ መኾናችሁንም ዕወቁ::))

ሱረቱል / አል በቀራህ 203

ዙልሒጃ አሥራ አንድ

ዙልሂጃ አሥራ ሁለት

ዙልሒጃ አሥራ ሦስት

**ሐጃጆች ማድረግ የሚገባቸው**

- ሚና በሚታደርበት ቀን ከቀትር በኋላ ሦስቱም ጀመራት ላይ ጠጠር መወርወር
- በእያንዳንዱ ጠጠር ውርወራ ላይ ተክቢራ ማሰማት
- ዱዓና ዚክር ማብዛት
- ሳይቻኮሉ ረጋ ብሎ ሥነ - ሥርዐት መጠበቅ
- ከጭቅጭቅ ከግፊያና ከፀያፍ ቃል መቆጠብ




# ጀመራት ላይ መወርወር

- ማንኛውም ሐጅ ትንሹንና መሐከለኛው ጀመራቶች ላይ ከወረወረ በኋላ ፊቱን ወደ ቂብላ አዙሮ እጆቹን ዘርግቶ ለማፊያና ለትርምር ሰበብ ሳይሆን የፈለገውን አይነት ዱዓ ማድረግ ሱና ነው ፡፡

> ትልቁ ጀመራት (ዓቀባ) ላይ ከተወረወረ በኋላ የሚደረግ ዱዓ የለም፡፡

- ዙልሒጃ አሥራሁለት ተቻኩሎ ሚናን ለቆ ለመውጣት የፈለገ ሦስቱም ጀመራት ላይ ጠጠር ወርውሮ ፀሐይ ከመግባቷ በፊት ሚናን ለቆ መውጣት አለበት ነገር ግን ሚናን ለቆ ከመውጣቱ በፊት ፀሐይ ከጠለቀችበት የግድ ዙልሒጃ አሥራ ሦስተኛው ቀን ሌሊት አድሮ ቀን ቀትር ላይ ሦስቱም ጀመራቶች ላይ ወርውሮ ሚናን ለቆ መውጣት ይኖርበታል፡፡

ሚናን ለመልቀቅ ተቻኩሎ ጉዞ ከጀመረ በኋላ ቢመሸበት ቀጥታ በመጓዝ ሚናን መልቀቅ አለበት መመለሱ ግዴታ አይሆንም፡፡



# የመሰናበቻ ጠዋፍ (ወዳዕ)


ሐጃጆች መሠረታዊ እና ግዴታ የሆኑትን የሐጅ ሥነ - ሥርዓቶች በጠቅላላ ካጠናቀቁ በኋላ ሚናን በመልቀቅ ጉዞ ወደ መከተል መክረማ በመጓዝ ሐረም መስጊድ በአላህ ጥንታዊው ቤት ካዕባ ዙርያ የመሰናበቻ ጠዋፍ ያደርጋሉ ይህም የረሱልን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ትዕዛዝ በማክበር ሲሆን ትዕዛዛቸውም ፡-

| |
|---|
| (አንዳችሁ የመጨረሻ ሥራውን በአላህ ቤት ሳያደርግ እንዳይጓዝ ብለዋል |

የመሰናበቻው ጠዋፍ ከሐጅ ግዴታዎች የመጨረሻው ነው ፡፡

ማንኛውም ሐጅ የመሰናበቻውን ጠዋፍ የሚያደርገው ወደ ሃገሩ ሊመለስ ሲል መሆን አለበት ፡፡

በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች ሲቀሩ የመሰናበቻ ጠዋፍ ማንኛውም ሐጅ መተው አይገባውም ፡፡



# የሐጅ መሰረቶችና ግዴታዎች


| 4 የሐጅ መሠረቶች (አርካን) | |
|---|---|
| 1 | ኢሕራም ማድረግ |
| 2 | ዓረፋ ላይ መቆም |
| 3 | ጠዋፍ (ጠዋፊል ኢፋዳ) |
| 4 | ሰዕይ ናቸው |

ከሐጅ መሠረቶች (አርካን) ) አንዱን ያጎደለ የጎደለውን እስካላሟላ ድረስ ሐጁ ሙሉ አይሆንም

| 7 የሐጅ ግዴታዎች (ዋጅብ) | |
|---|---|
| 1 | ከሚቃት ኢሕራም ማድረግ |
| 2 | ፀሐይ እስክትጠልቅ ዓረፋ ላይ መቆም |
| 3 | ሙዝደሊፋ ማደር |
| 4 | የአያመል ተሽሪቅ ሌሊቶችን ሚና ማደር |
| 5 | ጀመራት ላይ ጠጠር መወርወር |
| 6 | ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር |
| 7 | የመሰናበቻ ጠዋፍ ማድረግ |

ከሐጅ ግዴታዎች የተወ ማካካሻው መካ ላይ በግ አርዶ ለራሱ ሳይበላለት ለመካ ድሆች ያከፋፍላል።

# ሴቶቻችን ብቻ የሚመለከቱ መመሪያዎች



ለወንድም ሆነ ለሴት ሐጃጆች መሟላት ያለበት

ኢስላም መሆን

የአዕምሮ ጤነኛ

ለአካለ መጠን የደረሰ

ነፃ የሆነ (ባርያ ያልሆነ)

የገንዘብም ሆነ የጉልበት አቅም ያለው

ለሴት ባል ወይንም የሥጋ ዘመድ (መሕረም) መሟላት አለበት

ይኸውም ከሴቷ ጋር ለሐጅ መጓዝ የሚችሉት ፡- ባሏ ፣ ወይንም ዘላለም ሊያገቧት የማይችሉ ፡- አባቷ ፣ ልጇ ፣ ወንድሟ ፣ አጎቷ ፣ የጡት ወንድሟ ወይንም የናቷ ባልና የባሏ ልጆች የመሳሰሉት ናቸው ።

ለዚህም መረጃ ኢብኑ አባስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ከረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ኹጥባ ላይ እንደሰሙት ፡ - (አንድ ወንድ መሕረም ከሌላት ሴት ጋር ብቻቸውን እንዳይሆኑ ፡ ሴቷም ብትሆን የስጋ ዘመድ (የማያገባት) ሳይኖራት እንዳትጓዝ) ብለዋል፡፡
– አንድ ሰው ተነስቶ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ባለቤቴ ወደ ሐጅ ሄዳለች እኔ ደግሞ በእንዲህ አይነቱ ዘመቻ ተሳታፊ ነኝ አላቸው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ሂድ ከባለቤትህ ጋር ሐጅ አድርግ) አሉት፡፡

ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳሉት ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)

(መሕረም የሌላት ሴት ሦስት ቀን ለብቻዋ እንዳትጓዝ) ብለዋል፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት

ሴት ያለመሕረም ሐጅም ሆነ ወደ ሌላ ቦታ መጓዝ የሚከለክሉ ብዙ ሐዲሶች አሉ ሴት ያለ መሕረም ስትጓዝ ብቻዋን ልትቋቋመው የማትችለው ብዙ ችግርና አደጋ ሊገጥማት ይችላል ፡ በጉዞም ላይ የሚጠብቃት መሕረም ከሌላት በባለጌዎች በቀላሉ ልትጠቃ ትችላለች ።

# ለሴት መህረም የግድ ማሟላት ያለበት

ለሴት መሕረም የሚሆን ማሟላት ያለበት

ሙስሊም

የአዕምሮ ጤነኛ

ለአካለ መጠን የደረሰ

- ሴት መሕረም ካላገኘች ሐጇን በወኪል ማስደረግ ትችላለች
- ሴት ሐጅ ስታደርግ የሚከተሉትን ማክበር አለባት ፦

1 – የምታደርገው ሐጅ ፈርድ ሳይሆን ተጨማሪ (ነፍል) ከሆነ የግድ የባሏን ፈቃድ ማግኘት አለባት ፡ ባልም ተጨማሪ ሐጅ የምታደርግ ሚስቱን ከፈለገ ማስቀረት ይችላል ።

2 - ሁሉም ዓሊሞች እንደሚስማሙበት እንዲትሴት ሴት ልጇንም ሆነ ሌላ ሴት ለሐጅ እንደምትወክለው ሁሉ ወንድም ወክላ ሀጅ ማስደረግ ትችላለች።

3 - ሴት በሐጅ ጉዞ ላይ እያለች የወር አበባ ወይንም የወሊድ ደም ላይ ከሆነች ሐጇን በመቀጠል በካዕባ ዙርያ ጠዋፍ ማድረግ ብቻ ሲቀር ሌሎች ከወር አበባ የጠሩ ሐጃጅ ሴቶች የሚያደርጉትን ሁሉ ታደርጋለች ። በኢሕራም ኒያ ወቅት እንኳን ደም ቢመጣት ኢሕራም ማድረግ ትችላለች ፡ ኢሕራም ለማድረግ ከደም ንፁህ መሆን ግዴታ አይደለም።

4 - ሴት በኢሕራም ወቅት ወንዶች እንደሚያደርጉት ታደርጋለች ይኸውም ፦ መታጠብ ፣ ትርፍ ፀጉሮችን ማፀዳዳት ፣ ጥፍር መቁረጥ ፣ ልዩ መዓዛ (ሽታ) የሌለው ቅባት ሰውነቷን መቀባት ትችላለች ፡ ለዚሁም የሙእሚኖች እናት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) እንዳሉት፦

« ከረሱል (ሰለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም) ጋር ስንጓዝ በኢሕራም ወቅት ግንባራችን አካባቢ የተቀባነው ቅባት ቀልጦ በአንዳችን ፊት ላይ ሲፈስ ረሱል (ሰለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም) እያዩ አይከለክሉንም ነበር) ብለዋል ።

አቡ ዳውድ እንደዘገቡት

5 – ሴት ለኢሕራም ስትነይት ቡርቃ ወይንም ኒቃብ ፊቷን ሸፍና ከሆነ ማውለቅ አለባት ::
ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)

(ኢሕራም ላይ ያለች ሴት ፊቷን በኒቃብ አትሸፍንም) ብለዋል

ሴት ኢሕራም ላይ እያለች ባዕድ ወንድ አጠገብ ቡርቃና ኒቃብ ባልሆነ በሻሽ መሰል ጨርቅ (ኺማር) ፊቷን መሸፈን አለባት የእጇን መዳፎችም ቢሆን ጓንት ሳትለብስ በቀሚሷ እጅጌም ቢሆን መሸፈን ይገባታል ፡ ሴት ፊቷም ሆነ እጇ ባዕድ ወንድ ሊያየው የማይገባ ገላዋ ስለሆነ በሐጅም ሆነ በሌላ ቦታ መሸፈን ግዴታዋ ነው ::

ቡርቃ ፣
ኒቃብ ፣
የእጅ ጓንት

6 - ሴት በኢሕራም ወቅት የፈለገችውን አይነት የሴት ልብስ መልበስ ትችላለች :: ይኸውም ፡- ጌጣጌጥ የሌለበት ፣ ከወንድ ልብስ ጋር የማይመሳሰል ጠባብ ያልሆነ ፣ የሰውነቷን ቅርፅና ከውስጥ የለበሰችውን የማያሳይ ፣ ስስ ያልሆነ ፣ እግሯንና እጇን የማያሳይ አጭር ያልሆነ እንዲሁም ሰፊና እረዥም ቢሆን ይመረጣል ::

ለባዕድ ወንድ
የሚታይ
ጌጣጌጥና
ስስ ልብስ

– ብዙ ሙስሊም የዕውቀት ባለቤቶች እንደተስማሙበት ሴት በኢሕራም ወቅት መልበስ ያለባት እረዥም ቀሚስ ወይንም ሸሚዝ ፣ የውስጥ ሱሪ ፣ ሻሽ ፣ ሸፍንም ሆነ ነጠላ ጫማ ሲሆኑ የልብሷ መልክ የግድ ልዩ የሆነ ለምሳሌ አረንጓዴ መሆን የለበትም ማንኛ ውም አይነት መልክ ፡- አረንጓዴ ፣ ቀይም ሆነ ጥቁር ሊሆን ይችላል ፡ ከሌሎችም ጋር ተቀያይራ መልበስ ትችላለች ::

ሙግኒ - 3 / 328

በተልቢያ
ጊዜ ድምፅን
ከፍ ማድረግ

7 – ሴት ከኢሕራም ኒያ በኋላ ድምፂን ለራሷ ብቻ እንዲሰማ ዝቅ አድርጋ ተልቢያ ማለት ሱና ነው በድምፂ ወንዶችን ልትፈትን ስለምትችል ከፍ ማድረጉ ይጠላል ፡ ስለዚህም ነው ሴት አዛንም ሆነ ኢቃም የማትለው ፡ሴት በሰላት ወቅት ላይ ለመጠቆም እንደ ወንዶች ተስቢሕ ሳይሆን ጭብጨባ ነው የታዘዘችው ::

ሙግኒ 2 / 330 - 331

## ሴቶችን የሚመለከቱ የሐጅ መመሪያዎች

8 - ሴት በጠዋፍ ወቅት ሙሉ ሰውነቷን መሸፈን አለባት ፣ ድምጿን ዝቅ ፣ አይኗን ሰበር አድርጋ በተለይ ሐጀረል አስወድና ሩክነል የማኒ አካባቢ ከወንድ ሳትጋፋ ዳር ዳሩን ይዛ መጠወፍ አለባት ፡ ከወንዶች መሐል ገብታ ስትጋፋና ስትተሻሸ ወንዶች ላይ ፈተና ስለምታመጣ ሐራም ነው ፡ ከተመቸ ካዕባው አጠገብ ተጠግታ ሐጀረል አስወድ መሳም ሱና ነው ግን ለሱና ተብሎ በግፍያ ሐራም ውስጥ ላለመግባት መጠንቀቅ ያስፈልጋል ፡
ሐጀረል አስወድን ከሩቅ ካመላከተች በቂ ነው ፡፡

9 – ሴቶች በጠዋፍም ሆነ በሰዕይ ወቅት በእርጋታ መሄድ አለባቸው የዕውቀት ባለቤቶች እንደተስማሙበት ጠዋፍ ላይም ሆነ ሰፋ መርዋ ላይ መሮጥና ፣ የቀኝ ትከሻቸውን መግለፅ የለባቸውም፡፡

ሙግኒ - 3 / 324

10 -- ሴት በወር አበባ ላይ ስትሆንና ከጠራች በኋላ የምታደርገው፡
ሴት በወር አበባ ላይ እያለች ሁሉንም የሐጅ ሥነ - ሥርዓቶች ፡- ኢሕራም ፣ ዓረፋ ላይ መቆም ፣ ሙዝደሊፋ ማደር ፣ ጀመራት ላይ መወርወር ትችላለች ካዕባ ዙርያ ለምታደርገው ጠዋፍ ግን የግድ ከወር አበባ መጥራት አለባት ፡፡

ወንዶች መሃል መጋፋት

ሩጫ

የቀኝ ትከሻን መግለፅ

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለዓኢሻ (ረዲየሏሁ አንሃ) (ሐጃጆች የሚያደርጉትን ሁሉ አድርጊ እስክትጠሪ ድረስ ግን ካዐዕባን እንዳትጠውፊ ) ብለዋታል

ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት

ማስታወሻ...

-- ሴት ጠዋፍ ከጨረሰች በኋላ የወር አበባ ቢመጣባት ሳታቋርጥ ሰዕይ ማድረግ ትችላለች ፡ ሰፋ መርዋ ለመመላለስ ጡሃራ መሆን ግዴታ አይደለም ፡፡

ከኪታብ ሙዕሚናት ፡ ሼኽ ሳሊሕ ፈውዛን

11 - ሴቶች ሙዝደሊፋ በሚያድሩበት ሌሊት በድካም ምክንያት ግፍያውን ከፈሩ እኩለ ሌሊት ላይ ጨረቃ እንደጠለቀች ወደ ሚና መጊዝ ይችላሉ ሚና እንደደረሱ ትልቁ ጀመራት ላይ ሰባት ጠጠር ይወረውራሉ ::

12 - ሴት ለሐጅም ሆነ ለዑምራ የጣት አንጓ የሚያህል ከሙሉ የራስ ፀጉሯ ጫፍ ላይ ትቆርጣለች ሴት በሐጅ ሰበብ ሙሉ ፀጉሯን መላጩት አይፈቀድላትም::

አንጓ ማለት የአንድ ጣት የላይኛው ክፍል ነው

ደካሞች በጊዜ ይሄዳሉ

ፀጉር ማሳጠር ብቻ

በወር አበባ ምክንያት ጠዋፈል ወዳዕ ይነሳላታል


13 - በወር አበባ ላይ ያለች ሴት ትልቁ ጀመራት ላይ ጠጠር ወርውራ ፀጉሯን ከቆረጠች በኋላ ኢሕራሟ ስለሚፈታ ከባል ጋር ግብረ - ሥጋ ግንኙነት ሲቀር የኢሕራም ክልክሎች ሁሉ ይፈቀዱላታል ምናልባት ፀጉር ካሳጠረች በኋላ ከጠዋፈል ኢፋዳ በፊት ጠርታ ከባል ጋር ግብረ - ሥጋ ከፈፀመች ፊዲያ ግዴታ ይሆንባታል ይኸውም በግ አርዶ ለመካ ድሆች ማከፋፈል ነው ::

14 - ከጠዋፈል ኢፋዳ በኋላ የወር አበባ የመጣባት ሴት የመሰናበቻዉን ጠዋፍ ትታ ወደሀገሯ መመለስ ትችላለች ለዚሁም ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዓንሃ) ባወሩት ሐዲስ እንዲህ አሉ ሶፍያ ቢንት ሑያይ ጠዋፈል ኢፋዳ ካደረገች በኋላ የወር አበባ መጣባት ሁኔታዉንም ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ነገርኳቸዉ እሳቸዉም ታድያ ልታዘገየን ነዋ ?? አሉ እኔም የአላህ መልክተኛ ሆይ ጠዋፈል ኢፋዳ አድርጋለች እኮ አልኳቸዉ እሳቸዉም (እንግዲያዉስ ትጊዝ አሉ) ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት

ኢብኑ አባስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሰዎች የመጨረሻ ሥራቸው በአላህ ቤት እንዲሆን ሲያዝዙ በወር አበባና በወሊድ ደም ላይ ላሉ ሴቶች ብቻ አቀለሉላቸው:የመሰናበቻ ጠዋፍ ትተዉ መሄድ ይፈቀድላቸዋል » ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት

የሐጅና ዑምራ ማብራርያ

# የመዲና ዚያራ ሥነ - ሥርዓት



47

# የረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጊድ አዘያየር

መዲና ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የተሰደዱበት (ሒጅራ የወጡበትና) ተረጋግተው የኖሩባት ከተማ ነች።

መዲና የረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጊድ ያለበት ሲሆን መስጊዱም ከሦስቱ ለዒባዳ ጉዞ ከተፈቀደባቸው መስጊዶች አንዱ ነው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) (ለዒባዳ አስቦ ) ወደ ሦስቱ መስጊዶች በስተቀር ጉዞ እንዳታቀኑ) ብለዋል ፡፡
እነሱም

የሐረም መስጊድ (መካ)

ይህ መስጊዴ (መዲና)

የአቅሳ መስጊድ ፍልስጥኤም ናቸው ብለዋል

የረሱልን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጊድ መጎብኘት ከሐጅ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው እና ግዴታም አይደለም ወደ መዲና ሲኬድ ኢሕራም አይደረግም እመቱን ሙሉ በፈለጉት ወቅት መጎብኘት ይቻላል በአላህ ችሮታ ወደተከበሩት ሐረሞች መካና መዲና የደረሰ ወደ መዲና ሙነወራ የነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጊድ ውስጥ ለመስገድ መጓዝ ይወደዳል አግረ መንገዱንም ወደረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ቀብር ቀርቦ ሰላም ማለት ይፈቀዳል መዲና የነብዩ መስጊድ ውስጥ የተሰገደ ሰላት ሌላ ቦታ ከሚሰገድ ሰላት ሺ ጊዜ እጥፍ ይሆናል ፡



ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መካ ሐረም ላይ የተሰገደ ሰላት ሌላ ቦታ ከሚሰገድ ሰላት መቶ ሺ ጊዜ እጥፍ ይሆናል ብለዋል፡፡፡

# መዲና የመልዕክተኛው ከተማ

### ነብኚ የመልዕክተኛው መስጊድ እንደደረሰ

- ወደ መስጊድ በሚገባበት ጊዜ ቀኝ እግሩን አስቀድሞ በማስገባት እንዲህ ይላል

ቢስሚላህ ወሰላቱ ወሰላም ዓላ ረሱሉላህ

( አዑዙቢላሂል ዓዚም ወወጅሁሁል ከሪም ወሱልጣኑሁል ቀዲም ሚነሽይጧኒረጂም አላሁመ እፍታሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲከ)

ትርጉም ( በሃያሉ ጌታ የተከበረ ፊትና የነባር ስልጣን ባለቤት በሆነው አላህ)
ከእርጉሙ ሸይጧን ከፋት እጠበቃለሁ )

« አላህ ሆይ የእዝነትህን በር ክፈትልኝ »

- ይህ ዱዓ ማንኛውም መስጊድ ሲገባ ይደረጋል

### የመልዕክተኛው መስጊድ እንደተገባ

- መጀመሪያ ረከዓተይን ተሂየተል መስጊድ ይሰገዳል ሰላቱ የረውዳ ክልል ውስጥ ቢሆን ይመረጣል ያለበለዚያ የተገኘው ቦታ መስጊድ ውስጥ ሰግዶ ወደ ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ቀብር በመሄድ ፊቱን ወደ ቀብር አዙሮ በርጋታና በዝግተኛ ድምፅ ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሰላምታ ጀምሮ እንዲህ ይላል

««« አሰላሙ አለይከ አዩሀ ነብዩ ወራህመቱላሂ ወበረካቱሁ አላሁመ አቲሁ አል ወሲላ ወልፈዲላ ውብዓስሁ አልመቃመል መሕሙዳ አለዚ ወዓተሁ አላሁመ እጅዚሁ አን ኡመቲሂ አፍደል ጀዛዕ »»»

## የረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጊድ አዘያየር

- በመቀጠል ትንሽ ወደቀኝ ሄድ ብሎ « የአቢበክር አልሲዲቅ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ቀብር ፊትለፊት ቆሞ ሰላምታ አቅርቦ አላህ እዲምራቸዉ እንዲያዝንላቸዉና እንዲወዳቸዉ ዱዓ ማድረግ።
- እንደገና ትንሽ ወደቀኝ ሄድ ብሎ የዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ቀብር ፊትለፊት በመቆም ሰላምታ አቅርቦ አላህ እንዲምራቸዉ እንዲያዝንላቸዉና እንዲወዳቸዉ ዱዓ ማድረግ።

መጠንቀቅ የሚያስፈልገዉ

አንዳንድ የነብዩን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጊድ የሚዘይሩ ሰዎች የሚፈፅሙት ስህተት በኢስላም መሠረት የሌለዉ እና በሰሀቦችም(ረዲየሏሁ ዓንሁም) የማይታወቅ ድርጊት ነው

ከስህተቶቹም

- ✗ በቀብሩ ትንሽ መነካት እና በመስጊዱ ግድግዳ ዘርያ መተሻሸት
- ✗ በዱዓ ጊዜ ፊትን ወደ ቀብር ማዞር የመሳሰሉ ስህተቶች ይታያሉ፡
- ✓ ትክክለኛው መንገድ በዱዓ ጊዜ ፊትን ወደ ቂብላ ማዞር ብቻ ነው ።



## ለጎብኚዎች የሚፈቀዱ ሱናዎች

1- በቂዕ የሚባለውን መካነ መቃብርን መዘየር:- ምክንያቱም ብዙ ሰሐቦች የተቀበሩበት ሲሆን ከነሱም ውስጥ ሦስተኛዉ ኸሊፋ ዑስማን ኢብኑ ዓፋን (ረዲየሏሁ ዓንሁ) ይገኙበታል።

2 - የኡሁድ ሰማዕታትን (ሹሃዳዎች) መዘየር ከነሱም ውስጥ የሹሃዳዎች አለቃ ሐምዛ ቢን ኢብኑል ሙጠሊብ (የነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የአጎት ልጅ) ይገኙበታል ለሁሉም አላህ (ሥራቸውን) ይውደድላቸውና ሁሉንም ሰላም በማለት ረሱል (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ለሰሐባዎች በቀብር ላይ ያስተማሯቸውን ዱዓ ማድረግ ይኸውም:-

> አሰላም አለይኩም አህለ ዲያር ሚነል ሙእሚኒን ወል ሙስሊሚን ወኢና ኢንሻአላሁ ቢኩም ላሒቁን ነስአሉላሃ ለና ወለኩም አል አፍያ። ትርጉም :- አሰላም አለይኩም ከሙእሚኖችና ከሙስሊሞች ወገን የሆናችሁ የዚህ መካነ መቃብር ባለቤቶች ሆይ ለኛም ለናንተም አላህ ሰላሙን እንዲሰጠን እንለምነዋለን።

ሙስሊም እንደዘገቡት

ሌላው ሱና

3 ረሱል (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) እንዳደረጉት ወደ መስጊድ ቁባ ታጥቦ በመሄድ መስገድ ።

መስጂደል ቁባ በኢስላም መጀመርያ የተገነባ መስጊድ ነው በውስጡ የሚሰገደው ስላት ምንዳው :-

« ሱሄል ቢን ሐኒፍ (ረዲየላሁ ዓንሁ) እንዳወራው ረሱል (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) ( ከቤቱ ታጥቦ ወደ መስጊድ ቁባ በመሄድ የሰገደ ሰላቱ የዑምራን የሚያህል ምንዳ ያስገኝለታል ) ብለዋል ።

ሌላው ሁለት ትክክለኛ ሐዲሶች (ሰሒሐይን) ላይ ኢብኑ ዑመር እንዳወሩት « ረሱል (ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም) በግልቢያም ሆነ በእግር የቁባን መስጊድ ለመጎብኘት ሄደው ይሰግዱበት ነበር » ብለዋል

4 ከነዚህ መስጊዶች በስተቀር መዲና ውስጥ ሌላ የሚጎበኝ መስጊድም ሆነ ቦታ በኢስላም ሸሪዓ አይታወቅም ።

ስለዚህ :- ማንም ሰው ምንም ላይጠቅመው መዲና ውስጥ ወድያና ወዲህ በመመላለስ ጊዜውን ባያቃጥልና ባይለፋ ይሻለዋል ።

# የነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) መስጊድ



# አስፈላጊ ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)



# ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)

**ጥያቄ**

እንዳንድ ሰዎች በአውሮኘላን ለሚመጡ ሐጃጆች ጅዳ ሲደርሱ ኢሕራም እንዲያደርጉ ያዝዛሉ ሌሎች ደግሞ ጅዳ ላይ ኢሕራም ማድረግ ይቃወማሉ በዚህ ጉዳይ የትኛው ነው ትክክል ?

**መልስ**

– ሐጃጆች በጠቅላላ በአየር በባሕርም ሆነ በምድር ሲጓዙ ኢሕራም የሚያደርጉት በሚያቋርጡት ወይንም በሚቀርባቸው የሚቃት ክልል ላይ ነው ። ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የሚቃት ክልሎችን ሲወስኑ ( ሐጅና ዑምራ ለሚፈልግ የክልሉ ነዋሪዎች እንዲሁም በነሱ በኩል ለሚመጡ ) በማለት ገልፀዋል። ጅዳ ግን ከጅዳ ውጪ ለሚመጡ ሚቃት ሊሆን አይችልም ጅዳ ሚቃት የሚሆነው ለነዋሪዎቹና ለተለያየ ጉዳይ መጥተው ሐጅና ዑምራ ለሚፈልጉ ሙስሊሞች ብቻ ነው ።

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ ረሒመሁላህ

**ጥያቄ**

– አንድ ሰው ለራሱ ከዚህ በፊት ሐጅ አድርጎ ለሁለተኛ ጊዜ ሐጅ ለማድረግ ነይቶ ዓረፋ ከደረሰ በኋላ የሐጁን ኒያ ለዘመዱ መቀየር ይችላል ወይንስ አይችልም ?

**መልስ**

– አንድ ሰው ለራሱ ሐጅ ለማድረግ ነይቶ እሕራም ካደረገ በኋላ የትም ቦታ ቢሆን ለማንም ሰው ኒያውን መቀየር አይችልም ሐጁን ለራሱ መጨረስ አለበት ። አላህም በቁርአኑ

وَأَتِمُّوا۟ ٱلْحَجَّ وَٱلْعُمْرَةَ لِلَّهِ ۚ سورة البقرة ١٩٦

ትርጉም፡- ((ሐጅና ዑምራን ለአላህ ሙሉ)) ብሏልና አል በቀራህ- 196

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ ረሒመሁላህ

ለራሱ ኢሕራም ከነየተ ለራሱ መጨረስ ግዴታው ነው መጀመርያ ለራሱ ሐጅ ያደረገ ከሆነና ለሰው ከነየተ ለነየተለት ሰው መጨረስ ግዴታው ነው ፡

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ ረሒመሁላህ

**ጥያቄ**

እናቴ የሞተችው ገና ልጅ እያለሁ ነው በእናቴ ሥም ሐጅ የሚያደርግ ሰው ተከራይቻለሁ አባቴም ሲሞት አላውቅም ነበር ከዘመድ እንደሰማሁት ግን አባቴ ሐጅ አድርጓል ተብያለሁ አሁን ለወላጆቼ የግድ እራሴ ሐጅ ማድረግ አለብኝ ወይንስ ከፍዬ በሰው ማስደረግ እችላለሁ ::?

**መልስ**

በደንቡ መሰረት ለራስህ ሐጅ ካደረግክ በኋላ ደክመህም ቢሆን ለወላጆችህ ሐጅ ብታደርግላቸው የተሻለ ነው ያለበለዝያ ለሰው ከፍለህም ብታስደርግላቸው ይቻላል :: በተጨማሪ በኪራይ የወከልከውን ሰው ከሐጅ ጋር ዑምራም እንዲያደርግላቸው ማዘዝ መብትህ ነው ይህ ደግሞ ለነሱ በረካ ሲሆን የአንተም ሥራ ያማረ ይሆናል:: አላህ የኛንም የናንተንም ሥራ ይቀበል ::

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ ረሒመሁሏህ

**ጥያቄ**

አንዲት ሴት የመጀመርያ ፈርድ የሆነውን የሐጅ ሥነ - ሥርዓቶች በሚዝባ ፈፅማ ጠጠር ያስወረወረችው ግን በሰው ነው ምክንያቱም ሕፃን ልጅ ይዛ ነበርና በዚህ ጉዳይ ችግር አለው ወይ?

**መልስ**

፦ ምንም ችግር የለበትም በውክልና ማስወርወር ይቻላል በተለይ ለሴቶች ጀመራት ላይ መወርወር በጣም ከባድ ቦታ ነውና::

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ ረሒመሁሏህ

# ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)

**ጥያቄ**

አንድ ሰው በሕይወት እያለ በውክልና ለራሱ ሐጅ ማስደረግ ይችላል ?

**መልስ**

:- በሕይወት እያለ ለራሱ ሐጅ የሚያስደርግ ሰው በጣም ዕድሜው የገፋ ወይንም ሕመምተኛ ከሆነ በውክልና ሐጅ ማስደረግ ይችላል ከረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንደተረጋገጠው :- አንዱ ሰው ለአባቱ « አባቴ ሐጅ ማድረግም ሆነ መጊዝ አይችልም ሐጅ ላድርግለት? ብሎ ሲጠይቅ (ለአባትህ ሐጅም ዑምራም አድርግለት) ብለውታል ::
ሌላዋ ሴትዮ ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አባቴ ሐጅ ግዴታ ሆኖበታል ሐጅ ለማድረግ ጉልበት የለውም ስትላቸው (ለአባትሽ ሐጅ አድርጊ ) ብለዋታል ::

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ ረሒመሁሏህ

**ጥያቄ**

አንድ ሰው ሐጅ እንዲደረግለት ሳይናዘዝ ቢሞትና ከሞተ በኋላ ልጁ ሐጅ ቢያደርግለት ሚች ፈርድ የሆነው ሐጅ ይነሳለታልን?

**መልስ**

ሙስሊም ሆኖ ለራሱ ሐጅ ያደረገ ልጅም ሆነ ሌላ ሰው ለሚች ሐጅ ካደረገለት የሚች ፈርድ የሆነው ሐጅ ይነሳለታል በሐዲስ እንደተረጋገጠው ኢብኑ አባስ (ረዲየሏሁ ዓንሁ) እንዳወሩት ሴትየዋ ለረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ አባቴ ሽማግሌ በመሆኑ አላህ ፈርድ ያደረገውን ሐጅ ማድረግም ሆነ መንቀሳቀስ አይችልም እኔ ሐጅ ላድርግለትን ? ብላ ስትጠይቅ ( አዎን አድርጊለት) ብለዋታል ::

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ ረሒመሁሏህ

**ጥያቄ**

**እንድ ሐጅ የሚያደርግ ሰው ከጠዋፈል ኢፋዳ በፊት ሰዕይ ማድረግ ይችላል ?**

**መልስ**

የሐጁ አይነት ሙፍሪድ ወይንም ቃሪን ከሆነ ከጠዋፈል ኢፋዳ በፊት ከጠዋፈል ቁዱም በኋላ የሐጅን ሰዕይ ማድረግ ይቻላል ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የመስዋዕት ከብት ከነዱ ሰሐባዎች ጋር ከጠዋፈል ኢፋዳ በፊት የሐጅን ሰዕይ አድርገዋል ። ሐጁ ሙተመቲዕ ከሆነ ግን ሁለት ጊዜ ነው ሰዕይ መደረግ ያለበት ይኸውም

እንደኛው መካ እንደገባ ለዑምራ የሚያደርገው ሰዕይ ሲሆን ሁለተኛው ለሐጅ የሚያደርገው ሰዕይ ነው ለሐጅ የሚደረገው ሰዕይ ከጠዋፈል ኢፋዳ በኋላ ቢሆን ይመረጣል ምክንያቱም ሰዕዩ ለኢፋዳው ተከታይ ነውና ነገርግን ከጠዋፈል ኢፋዳ በፊት ሰዕይ ቢደረግም ምንም አይደለም ለዚሁም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ዘንድ አንድ ሰው ከጠዋፍ በፊት ሰዕይ አደረግኩኝ ሲላቸው ምንም አይደለም ብለውታል ።

ሐጅ የሚያደርግ ሰው የዒድ ቀን አምስት ሥራ መሥራት ይችላል

1 - ጀመረቱል ኩብራ ላይ ጠጠር መወርወር
2 - ማረድ
3 - ፀጉርን መላጨት ወይንም ማሳጠር
4 - ካዕባን መጠወፍ
5 - ሰዕይ ማድረግ ናቸው

– ሐጁ ቃሪን ወይንም ሙፍሪድ ከሆነና ከጠዋፈል ቁዱም በኋላ የሐጅ ሰዕይ ያደረገ ሲቀር ከላይ የተጠቀሱትን ቅደም ተከተል መጠበቅ የተሻለ ነው ። ቅደም ተከተሉን ማቀያየር ምንም ችግር የለበትም ።

## ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)

**ጥያቄ**

ለራሱ ዑምራ ካደረገ በኋላ በድጋሚ ለአባቱ ከተንዒም ኢሕራም ነይቶ ዑምራ ያደረገ ሰው ዑምራው ተቀባይነት አለውን? ወይንስ ለሐጅ ኢሕራም ያደረገበት ክልል መመለስ አለበት ?

**መልስ**

ለራስህ ዑምራ አድርገህ ኢሕራምህን ከፈታህ በኋላ በሞት ለተለዩ ወይንም ለደከሙ አባትህ ከፈለግክ ተንዒም ሄደህ ዑምራ ማድረግ ትችላለህ ወደ መጀመርያው የሚቃት ክልል መመለስ ግዴታ አይሆንብህም ::

በሳውዲያ የዓሊሞች ቋሚ ኮሚቴ

**ጥያቄ**

በኢሕራም ወቅት ድምፅን ከፍ አድርጎ መነየት ይበቃልን ?

**መልስ**

ሙስሊም በማንኛውም ሥራ ላይ ድምፁን አሰምቶ መነየት የለበትም ፡ ከነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንደተገኘው ኢሕራም ላይ ብቻ ድምፅን ከፍ አድረጎ መነየት ይቻላል ፡ በሰላትና በጠዋፍ ላይ ግን በኒያ ወቅት ፈፅሞ ድምፅን ማሰማት የለበትም ይህን ያህል ልሰግድ ነይቻለሁ ይህን ያህል ልጠውፍ ነይቻለሁ ማለቱ በዲን ላይ ፈጠራ (ቢድዓ) ነው በሰላትና በጠዋፍ ወቅት ድምፅ አሰምቶ መነየት የሚፈቀድ ቢሆን ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለዑመታቸው ይገልፁት ነበር ሰለፎችም ከሁሉም በፊት ይከተሉ ነበር ::

እንግዲህ ከነብዩም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሆነ ከሰሐባዎች ያልተገኘ ነገር በዲን ላይ መጨመር ፈጠራ (ቢድዓ) ነው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል :-

> (ከሁሉም ነገር የተጠላው መጥፎ ወሬ ነው መጥፎ ወሬ ደግሞ ፈጠራ ነው ፈጠራ ደግሞ ጥመት ነው ) ሙስሊም

> ሌላው ሐዲስ (ከዲን ያልሆነ ነገር በዲናችን ላይ የፈጠረ (ወደራሱ ተመላሽ ነው) ተቀባይነት የለውም) ቡኻሪና ሙስሊም የተስማሙበት ሐዲስ

> ሌላው (ከዲናችን ያልሆነ ሥራን የሠራ ሥራው ተመላሽ ነው ) ሙስሊም ዘግበውታል

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

**ጥያቄ**

የማጠቃለያ ጠዋፍ (ጠዋፊል ኢፋዳ) ጋር አብሮ በኒያ የመሰናበቻ ጠዋፍ (ጠዋፊል ወዳዕ) አድርጎ ወድያውኑ ወደመጡበት ሃገር መመለስ ይቻላልን ?

**መልስ**

ምንም ችግር የለበትም የሐጅን ሥራ ሁሉ አጠናቆ ጠዋፊል ኢፋዳ የቀረበት ሰው ለመሳፈር ከቸኮለ ጠዋፊል ኢፋዳና ጠዋፊል ወዳዕ በአንድ ላይ ነይቶ መጠወፍ ይችላል ። ለየብቻ መጠወፉ ግን የበለጠ ምንዳ ያስገኛል ። ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

**ጥያቄ**

እኔ የምኖረው ጅዳ ከተማ ውስጥ ነው ሰባት ጊዜ ሐጅ አድርጊያለሁ ታድያ አንድም ጊዜ የመሰናበቻ ጠዋፍ (ጠዋፊል ወዳዕ) ጠውፌ አላውቅም ምክንያቱም ሰዎች ለጅዳ ነዋሪ የመሰናበቻ ጠዋፍ የለውም ሲሉ ስምቻለሁ ታድያ ሐጄ ትክክል ነው ወይንስ እንዴት ነው ?

**መልስ**

የጅዳ ነዋሪዎችም ሆኑ ሌሎች ከሐጅ መልስ የመሰናበቻ ጠዋፍ ማድረግ ግዴታቸው ነው መረጃውም ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሐጃጆች ዳስኩር (ኹጥባ) ሲያደርጉ

( ማናችሁም ብትሆኑ የመጨረሻ የሐጅ ሥራችሁ በአላህ ቤት ሳታደርጉ እንዳትጓዙ) ይሉ ነበር ሙስሊም ሰሒሕ

ሰሒሐይን ሐዲስ ላይ ኢብኑ አባስ እንዲህ ብለዋል

(ሰዎች የመጨረሻ የሐጅ) ሥራቸው በአላህ ቤት እንዲሆን ሲታዘዝ በወር አበባ ላይ ላሉ ሴቶች ብቻ ቀለለላቸው) ብለዋል

ጠዋፊል ወዳዕ የተወ ሐጅ ማረድ ግዴታ ይሆንበታል እርዱም በግ ወይንም ፍየል ሲሆን ለሰባት ሆኖ ግመል ወይንም በሬ ማረድ ይቻላል የታረደውንም ለመካ ድሆች አከፋፍሎ ከፀፀት ጋር እስቲግፋር ማድረግ አለበት።

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

# ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)

ጥያቄ

መልስ

አንድ ሰው ለምሳሌ ጠዋፍ ሲያደርግ አምስተኛው ዙር ግማሽ ላይ እያለ ፈርድ ሰላት ጀምዓ ለመስገድ ጠዋፉን ቢያቋርጥ ከሰላት በኋላ አምስተኛውን ዙር ካቆመበት ቦታ ነው የሚቀጥለው ወይንስ ግማሹን ዙር ሰርዞት እንደገና ከሐጀረል አስወድ እንደ አዲስ መጀመር አለበት ?

በእንደዚህ አይነት አጋጣሚ ግማሹ ዙር መሰረዝ የለበትም ከኢማም ጋር ለመስገድ ጠዋፍን ካቋረጡ ሰላቱ ሲያበቃ ካቋረጡበት ቦታ ነው መጀመር ያለበት።

በሳዑዲያ የዓሊሞች ቋሚ ኮሚቴ

ጥያቄ

መልስ

እኛ አውስትራሊያ የምንኖር ሙስሊሞች በዚህ ዓመት ብዙ ሆነን ፈርድ የሆነውን ሐጅ ለማድረግ ስለምንፈልግ ተንስተናል ጉዟችንም ለምሳሌ የመጀመርያ መነሻችን ሲድኒ ከተማ ከሆነ በአየር የምናልፍባቸው ከተሞች አቡዳቢ ፣ ባህሬን ፣ ጅዳ ናቸው ታድያ ኢሕራም የምናደርግበት ሚቃታችን የት ነው ? ሲድኒ ከተማ ላይ ነው ኢሕራም የምናደርገው ወይንስ ያገኘነው ቦታ ላይ ነው ?

ሐጅም ሆነ ዑምራ ለሚያደርጉ ሁሉ ሲድኒ አቡዷቢም ሆነ ባህሬን ሚቃት ሲሆኑ አይችሉም ጅዳም ቢሆን ለነዋሪዎቹ ነው እንጂ ለእንደናንተ አይነቱ ሚቃት አይሆንም ።
ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የሚቃት ቦታዎችን ሲጠቁሙ.
(ሐጅና ዑምራ ለሚፈልግ ለክልሉ ነዋሪዎች እንዲሁም በነሱ በኩል ለሚያልፉ) ብለው ወስነዋል ። ስለዚህ አየር ላይ ሆናችሁ የምታልፉበትን የሚቃት ክልል ለአስተናጋጆች መጠየቅ አለባችሁ የሚቃትን ክልል ኢሕራም ሳናደርግ እናልፈዋለን ብላችሁ ከሰጋችሁ መጀመርያ የሚቃት ክልል ሳትደርሱ ለዑምራም ሆነ ለሐጅ ኢሕራም መነየት ትችላላችሁ ።
ለኢሕራም ለመዘጋጀት መታጠቡን ፣ መበጻጀቱንና የኢሕራም ልብስ መልበሱን የተመቻቻሁ ቦታ ማድረግ ትችላላችሁ ።



በሳዑዲያ የዓሊሞች ቋሚ ኮሚቴ

ጥያቄ

ቂራን ነይቶ ሐጅና ዑምራን አንድ ላይ አድርጎ በግ አርዶ ሳያበላ ሳይፆምም መካን ለቆ ራቅ ወዳለ ቦታ የተጓዘ ምን ማድረግ አለበት ?

መልስ

ማረድ ግዴታው ነው እራሱም ሆነ ሌላ ታማኝ ወኪል መከተል ሙከረማ ላይ ለቂራን ብሎ አርዶ ለመካ ድሃዎች አከፋፍሎ ለራሱም በልቶለት ለፈለገውም ከዛው ላይ ለስጦታ መቀነስ ይችላል ፡ እርዱን ካልቻለ ባለበት ቦታ አስር ቀን መፃም አለበት ።

በሳዑዲያ የዓሊሞች ቋሚ ኮሚቴ

ጥያቄ

አንድ ሐጅ አድራጊ የሐጅ መሠረቶችንና ግዴታዎችን ሁሉ አጠናቆ ጠዋፈል ኢፋዳና ጠዋፈል ወዳዕ ብቻ ቀርቶት የሐጅ መጨረሻ ቀን ወይንም አያመል ተሽሪቅ ሁለተኛው ቀን ጠዋፈል ኢፋዳ አድርጎ በኒያ ለጠዋፈል ወዳዕም ይሆነኛል ብሎ ከሳዑዲ አረቢያ ውጪ ወደሚኖርበት ሃገር ቢመለስ ይበቃለታልን ?

መልስ

ጉዳዩ እሱ እንደሚለው ሆኖ ጠዋፈል ኢፋዳ አድርጎ በቀጥታ መካ ከተማን ለቆ የሚወጣ ከሆነ ይበቃለታል ምክንያቱም ጠዋፈል ኢፋዳ ሲነየት ለኢፋዳም ለወዳዕም ብሎ መነየት ይችላል ከዛ በፊት ግን ለመጨረሻ ጊዜ ጀመራቶች ላይ ሁሉ ከወረወረ በኋላ መሆን አለበት፡፡

በሳዑዲያ የዓሊሞች ቋሚ ኮሚቴ

# ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)

**ጥያቄ**

መፍሪድ ሆኜ ሐጅ ሳደርግ ዓረፋ ከመሄዴ በፊት ጠዋፍና ሰዕይ ካደረግኩኝ በኋላ ከዐረፋ ስመለስ ከጠዋፈል ኢፋዳ ጋር ሰዕይ ማድረግ ይገባኛል ወይ ?

**መልስ**

ሐጁ ሙፍሪድ ስለሆን በዚህ በቂ ነው ፡ ዑምራና ሐጅን አቆራኝቶ ቃሪን የነየተ ከሆነም መካ እንደደረሰ ጠዋፍና ሰዕይ አድርጎ በኢሕራሙ ከቆየ ሙፍሪድም ሆነ ቃሪን ኢሕራሙን ሳይፈታ ያደረገው ሰዕይ በቂ ነው ሌላ ሰዕይ የለባቸውም እስከ ዙልሒጃ ስምንት ኢሕራሙን ሳይፈታ የዒድ ቀን የሚያደርገው ጠዋፈል ኢፋዳ ብቻ ይበቃዋል ። ቃሪን ከሆነ የመስዋዕት ከብቱን (ሐዲይ) ካረደ በኋላ ጠዋፈል ኢፋዳ ብቻ ነው የሚያደርገው።
ሁለት ጊዜ ሰዕይ ማድረግ የሚገባው ዑምራና ሐጅን እንድ ላይ የሚያደርግ (ሙተመቲዕ) የነየተ ብቻ ነው ። ይኸውም ፦ ለዑምራ ነይቶ ጠዋፍና ሰዕይ ካደረገ በኋላ ኢሕራሙን ፈትቶ እንደገና ለሐጅ ኢሕራም ሲያደርግ ሌላ የሐጅ ሰዕይ ይኖርበታል ።

በሳዑዲያ የዓሊሞች ቋሚ ኮሚቴ

**ጥያቄ**

ሐጅም ዑምራም ሳይፈልግ ወደ መካ መጊዝ ምን ችግር አለበት ?

**መልስ**

ሐጅም ሆነ ዑምራ ሳይፈልግ ወደ መካ የሚገባ ነጋዴ ፣ ሠራተኛ ፣ ፖስተኛ ፣ ሾፌርም ሆነ ሌሎች በፍላጎታቸው ካልሆነ በስተቀር መካ ስለሚገቡ የግድ ኢሕራም ያድርጉ አይባልም። ሐዲስ ሰሒሕ ላይ እንደተዘገበው ረሱል (ሰለሳሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳብራሩት (ለሚቃት ክልል ነዋሪዎችና ከነሱ ወገን ሳልሆኑ በነሱ በኩል ለሚያልፉ ሐጅና ዑምራ ለሚፈልግ ) ብለዋል ። ከዚህ የምንረዳው በሚቃት በኩል የሚያልፍ ሐጅም ሆነ ዑምራ የማይፈልግ ከሆነ ያለኢሕራም ማለፍ ይቻላል ማለት ነው ። ይህም አላህ ለባርያው ስለሚያዝን አግርቶለት ነው ።

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

**ጥያቄ**

**መልስ**

**ሙተመቲዕ ወይንም ቃሪን የሆን ሐጅ ለመስዋዕት (ሐድይ) የሚሆን እርድ ካላገኘ ምን ማድረግ አለበት ?**

ሙተመቲዕ ወይንም ቃሪን ሆኖ ማረድ ያልቻለ የግድ ሦስት ቀን ሐጅ ላይ ሰባት ቀን ወደ ቤተሰቡ ሲመለስ ባጠቃላይ አሥር ቀን መፆም አለበት ሐጅ ላይ የሚፆማቸውን ሦስት ቀኖች ከፊስን ከዙልሒጃ ስምንት በፊት ወይንም ሦስቱን አያመል ተሽሪቅ መፆም ምርጫ አለው አላህም በቁርአኑ ሲገልፅ :-

١٩٥ وَأَتِمُّوا۟ ٱلْحَجَّ وَٱلْعُمْرَةَ لِلَّهِ ۚ فَإِنْ أُحْصِرْتُمْ فَمَا ٱسْتَيْسَرَ مِنَ ٱلْهَدْىِ ۖ وَلَا تَحْلِقُوا۟
رُءُوسَكُمْ حَتَّىٰ يَبْلُغَ ٱلْهَدْىُ مَحِلَّهُۥ ۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوْ بِهِۦٓ أَذًى مِّن رَّأْسِهِۦ فَفِدْيَةٌ
مِّن صِيَامٍ أَوْ صَدَقَةٍ أَوْ نُسُكٍ ۚ فَإِذَآ أَمِنتُمْ فَمَن تَمَتَّعَ بِٱلْعُمْرَةِ إِلَى ٱلْحَجِّ فَمَا ٱسْتَيْسَرَ مِنَ ٱلْهَدْىِ ۚ
فَمَن لَّمْ يَجِدْ فَصِيَامُ ثَلَٰثَةِ أَيَّامٍ فِى ٱلْحَجِّ وَسَبْعَةٍ إِذَا رَجَعْتُمْ ۗ تِلْكَ عَشَرَةٌ كَامِلَةٌ ۗ ذَٰلِكَ
لِمَن لَّمْ يَكُنْ أَهْلُهُۥ حَاضِرِى ٱلْمَسْجِدِ ٱلْحَرَامِ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ

ትርጉም ((ሐጅንና ዑምራንም ለአላህ ሙሉ ብትታገዱም ከሃድይ (ከመሥዋዕት) የተገራውን (መሠዋት) አለባችሁ ሀድዩም እስፍራው እስከሚደርስ ድረስ ራሶቻችሁን አትላጩ ከእናንተ ውስጥ በሽተኛ ወይም በራሱ እውከት ያለበት የኾነ ሰው (ቢላጭ) ከፆም ወይም ከምፅዋት ወይም ከመሥዋዕት ቤዛ አለበት ፀጥታም ባገኛችሁ ጊዜ እስከ ሐጅ በዑምራም የተጣቀመ ሰው ከሓድይ የተገራውን (መሠዋት) አለበት ያላገኘም ሰው ሦስትን ቀኖች በሐጅ ወራት ሰባትንም በተመለሳችሁ ጊዜ መፆም አለበት ይህች አሥር (ቀናት) ናት ይህም (ሕግ) ቤተሰቦቹ ከክልሉ መስጊድ አቅራቢያ ላልሆኑ ነው አላህንም ፍሩ አላህም ቅጣተ ብርቱ መሆኑን ዕወቁ ::)) ሱረቱል አል በቀራህ 195 ቡኻሪ ላይ አሙል ሙእሚን ዓኢሻ እና ኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዓንሁም)

(አያመል ተሽሪቅ መፆም ለማንም አልተፈቀደም መስዋዕት (ሐድይ) ማቅረብ ላልቻለ ብቻ ሲቀር) ብለዋል ::

– የፊስን ከዓረፋ ቀን በፊት ሦስት ቀኖች መፆም የተመረጠ ነው ምክንያቱም የዓረፋ ቀን ማፍጠሩ ሱና ነው ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የዓረፋ ቀን ዓረፋ ላይ አፍጥረዋል መፆምም ከልክለዋል ሦስቱን የተጠቀሱትን ቀኖችም ሆኑ ወደ ሀገር ሲመለሱ የሚፆሙት ሰባት ቀኖች አከታትሎም ሆነ አለያይቶ መፆም ይቻላል ::

وَسَبْعَةٍ إِذَا رَجَعْتُمْ

ማረድ ያቃተው ለማረጃ ሰውን ከመለመን አሥር ቀን መፆሙ የተሻለ ነው:: ከኪታብ ተሕቂቅ ወልኢዷህ

## ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)

**ጥያቄ**

በሐጅ ወቅት ሴት የወር አበባ ለጊዜው እንዲቆምላት ወይንም እንዲዘገይላት ኪኒን መጠቀም ትችላለችን ?

**መልስ**

ሴት በሐጅ ወቅትም ሆነ በረመዳን ከሰው ጋር ለመፆም የወር አበባን የሚያቆም ኪኒን መጠቀም ትችላለች ኪኒን ከመውሰዷ በፊት ግን የህክምና ባለሙያ ማማከር አለባት።
ጥያቄ

**ጥያቄ**

ከሐጅ ወሮች በፊት ሚቃት የደረሰ ምን ማድረግ አለበት ?

**መልስ**

ሚቃት የደረሰ ሰው በሁለት መልኩ ይታያል :-

አንደኛ -- ከሐጅ ወሮች ውጪ ለምሳሌ በሻዕባንና በረመዳን ሚቃት የደረሰ ትክክለኛው ሱና ለዑምራ ብሎ ኢሕራም አድርጎ በልቡ ነይቶ ለበይክ ዑምራ ወይንም አላሁመ ለበይክ ዑምራ በማለት ደጋግሞ ተልቢያ ይላል መካ የአላህ ቤት እንደደረሰ ካዕባውን ሰባት ጊዜ ይጠውፈውና መቃመ ኢብራሂም አካባቢ ረከዓተይን ሰግዶ ሰዕይ ለማድረግ ወደ ሰፋ መርዋ መመላለሻ ይሄዳል ሰዕዩን እንደጨረሰ የራስ ፀጉሩን ተላጭቶ ወይንም አሳጥሮ ዑምራው ተጠናቀቀ ማለት ነው በመቀጠል በኢሕራም ወቅት የተከለከሉት ሁሉ ይፈቀዱለታል።

ሁለተኛ -- በሐጅ ወሮች ማለትም ሸዋል ፣ ዙልቃዕዳ እና የመጀመርያዎቹ የዙልሒጃ ዘጠኝ ቀኖች አሥረኛውን ሌሊት ጨምሮ ሚቃት የደረሰ ሦስት አይነት አማራጮች አሉት ይኸውም ሐጅን ለብቻ ማድረግ ፣ ዑምራ ለብቻ ማድረግ፣ ሐጅና ዑምራን አንድ ላይ ማድረግ ናቸው።

ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በዙልቃዕዳ ወር የመሰናበቻውን ሐጅ ለማድረግ ሚቃት ሲደርሱ ለሶሐቦቻቸው ሦስቱን የሐጅና ዑምራ አፈፃፀም (ኑሱክ) ነው ያስመረጧቸው :
-ሌላው ከሐጅ ወሮች ውጪ ሚቃት የደረሰ ከብት ያልነዳ ከሆነ ለዑምራ ነይቶ በተብራራው መሠረት ይፈፅማል ረሱልም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ለሶሐቦቻቸው ወደ መካ ሲቃረቡ ከብት ላልነዱት ኢሕራማቸውን ለዑምራ እንዲያደርጉ በማዘዝ መፈቀዱን አረጋግጠውላቸዋል ፡፡

ከኪታብ ተሕቂቅ ወልኢዷህ በሼኽ ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

**ጥያቄ**

እናቴ ዕድሜዋ የገፋ ቢሆንም ሐጅ ለማድረግ ትፈልጋለች ነገር ግን አብሯት የሚጓዝ የስጋ ዘመድ (መሕረም) የላትም መሕረም ቢገኝም ወጪው በጣም የናረ ነው ይከብዳል ታድያ ምን ማድረግ አለብን ?

**መልስ**

ሴት በዕድሜዋ አረጋዊ ሆነችም ወጣት ያለመሕረም ሐጅም ቢሆን መሄድ አይፈቀድላትም ስለዚህ ሐጅም ግዴታ አይሆንባትም ፡ ከመሕረም ጋር ለመጓዝ ከተሳካላት ሐጅ ማድረግ አለባት ምናልባት ሐጅ ሳታደርግ ከሞተች በገንዘቧ ሐጅ ማስደረግ ይቻላል ወይንም አንድ ዘመዷ ገንዘቡን ለግሶ ሐጅ ቢያስደርግላት በጣም የተወደደ ሥራ ነው።

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

**ጥያቄ**

በእንዴት አይነት ሁኔታ ነው በወኪል ማስወርወር የሚቻለው ? ለመሆኑ በወኪል ማስወርወር የማይቻልበት ቀን አለ ወይ ?

**መልስ**

ሁሉም ጀመራቶች ላይ በውክልና ማስወርወር ይቻላል እነሱም - ለሕመምተኛ ፣ ለደካማ ፣ ለደህንነቷ የምትሰጋ እርጉዝ ሴት ፣ ሕፃን የሚጠብቅላት የማታገኝ እጥቢ እናት ፣ — ሽማግሌዎችና አረጋውያን ሲሆኑ ሐጅ ለሚያደርጉ ሕፃናትም አሳዳጊዎቻቸው ወይንም ጠባቂዎቻቸው ሊወረውሩላቸው ይችላሉ።

– ውክልና ወስዶ የሚወረውረው ሰው በአንዱ ጀመራት ላይ መጀመርያ ለራሱ ወርውሮ በማስከተል ለተወከለው ሰው ይወረውራል በዚህ መልኩ ሁሉንም ጀመራት ያዳርሳል ።

– ውክልናውን ወስዶ የሚወረውረው ሰው የሚያደርገው ሐጅ ፈርድ ሳይሆን ተጨማሪ (ነፍል) ከሆነ ውርወራውን ከራሱም ሆነ ከተወከለለት ሰው ቢጀምር ምንም ለውጥ የለውም ዋናው መዘንጋት የሌለበት ውክልናውን ወስዶ የሚወረውረው ሰው ሐጅ እያደረገ መሆን አለበት በወቅቱ ሐጅ ያላደረገ ሰው ለሐጃጆች ውክልና ወስዶ መወርወር አይችልም ።

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

# ጥያቄና መልስ (ፈታዋ)

**ጥያቄ**

በወር አበባ ወቅት ሳልጠራ አንዳንድ የቁርአን ተፍሲሮችን አነባለሁ ለመሆኑ ችግር አለበትን ? በዚህ ሥራዬስ ወንጀለኛ እሆናለሁ ?

**መልስ**

ብዙ ዓሊሞች እንደሚስማሙበት በወር አበባና በወሊድ ደም ወቅት ያሉ ሴቶች ማንኛውንም አይነት ኪታብ መቅራት ሲችሉ ቁርአንንም ቢሆን ገፁን ሳይነኩት በቃላቸው መቅራት ይችላሉ ። ቁርአንን ፈፅሞ መቅራት የማይችለው ጁኑብ የሆነ ሰው ነው ጁኑብም ቢሆን ግን ምናልባት ከቁርአን አንቀፅ ከመሐሉ መቅራት ይችላል ።

በሐዲስ እንደተረጋገጠው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ከጀናባ በስተቀር ቁርአን ለመቅራት የሚያግዳቸው ነገር አልነበረም።

**ጥያቄ**

ዑምራ በማደርግበት ጊዜ ክልክል መሆኑን ሳላውቅ ሴቶች ፊታቸውን የሚሸፍኑበትን ቡርቃ (ኒቃብ) ለበስኩኝ ታድያ አሁን ለስህተቴ ማካካሻው (ከፋራው) ምንድን ነው ?


**መልስ**

ቡርቃ (ኒቃብ) ሴቶች ፊታቸውን የሚሸፍኑበት በአናት የሚታሰር ጨርቅ በኢሕራም ወቅት ክልክል ነው ፡ በኢሕራም ወቅት ኒቃብ የለበሰች ሴት ፊዲያ ግዴታ ይሆንባታል ይኸውም በግ ማረድ ወይንም ስድስት ምስኪን ማብላት ወይንም ሦስት ቀን መፆም ናቸው ነገር ግን ፊዲያውን ለመካስ ቅድመ ሁኔታ (ሸርጥ) አለው ሸርጡም በኢሕራም ወቅት ኒቃብ ያደረገችው ሸሪዓዊ ደንቡን ባለማወቅ ወይንም እረስታ ከሆነ ፊዲያ መካስ የለባትም ፊዲያ ግዴታ የሚሆንባት በኢሕራም ወቀት ክልክሉችን አውቆ የተዳፈረ ብቻ ነው ።

ዓብዱል ዓዚዝ ቢን ባዝ

የሐጅና ዑምራ ማብራርያ

# ዱዓ



# ዱዓ

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንዳሉት ምርጥ ዱዓ ማለት የዓረፋ ቀን ዱዓ ሲሆን እኔና ነብያቶች ከተናገርናቸው ምርጥ ቃል ብለው የሚከተሉትን ጠቅሰዋል:- ላኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላሸሪከለሁ
ለሁልሙልኩ ወለሁል ሐምዱ
ዩሕዪ ወዩሚቱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር

ሌላው በሐዲስ እንደተረጋገጠው ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አላህ ዘንድ የተወደዱት ቃሎች አራት ናቸው :- ብለዋል:: እነሱም:-

ሱብሐነሏህ ወልሐምዱ ሊላህ
ወላኢላሃ ኢለሏህ ወሏሁ አክበር

-- ይህንን ዚክር ሃሳብ ሳይባክን በጥሞና መደጋገም የተወደደ ነው ::
በተጨማሪ በዚህ በተከበረው ቀን የታወቁ ዱዓዎችንና ዚክሮችን ማብዛት በጣም ተገቢ ነው::
ከዱዓዎችም :–

- ሱብሐነሏህ ወቢሐምዲሂ ሱብሐነሏሂል ዓዚም
- ከጉድለት የጠራው አላህ ምስጉን ነው የጠራው አላህ ክቡር ነው –
ላኢላሃ ኢላ አንተ ሱብሐነከ ኢኒ ኩንቱ ሚነዟሊሚን
- ካንተ በሥተቀር ጌታ የለም የጠራህ (አላህ) ሆይ እኔ ከበዳዮች ነኝ
- ላኢሏሃ ኢለላህ ወላነዕቡዱ ኢላ ኢያሁ ለሁ ኒዕማ ወለሁል ፈድል ወለሁል ሰናእል ሐሰን

– ከአላህ በስተቀር ጌታ የለም ከሱ በስተቀር ማንንም አንገዛም ፀጋ በረከትና ውዳሴ ለሱ ብቻ ነው

- ላኢላሃ ኢለሏህ ሙኽሊሲነ ለሁዲነ ወለው ኩሪሃል ካፊሩን ::
- ከአላህ በስተቀር ጌታ የለም ምንም እንኳን ካፊሮች ቢጠሉም ሃይማኖት ፍፁም ለሱ ብቻ ነው
ላሐውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ
አላህ የሌለበት ሐይልም ሆነ ጥንካሬ የለም
- ረበና አቲና ፊዱንያ ሐሰነተን ወፊል አኺረተ ሐሰነተን ወቂና አዛበናር ::

ጌታችን (አላህ) ሆይ በዱንያ ያማረውን ስጠን በአኼራም ያማረውን ስጠን ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን ::

وَقَالَ رَبُّكُمُ ادْعُونِي أَسْتَجِبْ لَكُمْ ۚ إِنَّ الَّذِينَ يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِي سَيَدْخُلُونَ جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ ٦٠

ትርጉም **((ጌታችሁም አለ :- ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና እነዛ እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሃነምን በእርግጥ ይገባሉ::))** ሱረቱል አል ጋፊር 60

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ( ሃያሉ ጌታችሁ የሚያፍር ለጋሽ ነው ወደ እሱ የተዘረጉ የባርያውን እጆች ባዶውን መመለስ ያፍራል )ብለዋል

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሙስሊም በዱዓው ውስጥ ዘመድ መቁረጥና ወንጀል ሳይቀላቅል ሲለምን ከሦስት ነገር አንዱን ሳይሰጠው አይቀርም (ይኸውም) ዱዓው ውጤቱ ይዘጋያል 1 ወይንም ለአኼራው ይቀመጥለታል 1 ወይንም የዱዓው ተመጣጣኝ የሆነ አደጋ ይመከትለታል::

ሰሐቦችም ታድያ ዱዓ እናብዛ ? ሲሉ አላህ ውዳሴው የበዛ ነው አሏቸው

# የዱዓ ሥነ ሥርዓት

- ፍፁም ለአላህ መሆን
- ዱዓ ሲጀምሩና ሲጨርሱ አላህን እያመሰገኑና እያወደሱ በረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ላይ ሰላዋት ማውረድ ፡፡
- ሳይጠራጠሩ በፅኑ አቋም ዱዓዬን ይቀበለኛል ብሎ መመኘት
- በዱዓ ወቅት ልብን መሰብሰብ
- በችግርም ሆነ በደስታ ጊዜ ዱዓ ማብዛት
- ከአላህ በስተቀር ወደ ማንም ዱዓ ያለማድረግ
- በራስ ላይ በቤተሰብ በልጅና በንብረት ላይ መጥፎ ዱዓ ያለማድረግ
- ድምፅን ዝቅ አድርጎ ሳይጮሁ በአላህ ፍራቻ ዱዓ ማድረግ
- በስሩት ወንጀል ጥፋተኛነትን አምኖ ለአላህ ምህረት መጠየቅ ያገኙትንም ፀጋ ከአላህ መሆኑን አውቆ ማመስገን
- በዱዓ ወቅት ከይዩልኝ መራቅ ከሁሉም ሀሳብ ነፃ ሆኖ በተመስጦ በተስፋና በፍራቻ ዱዓ ማድረግ
- የበደሉትን ሰው በደሉን መካስና ተውበት ማድረግ
- ዱዓን ሦስት ጊዜ መደጋገም
- በዱዓ ጊዜ ሁለት እጆችን መዘርጋት
- ከተመቸ በዱዓ ጊዜ ውዱዕ ማድረግ
- በዱዓ ጊዜ ረጋ ብሎ ከአላህ ጋር ሥነ - ሥርዓት መጠበቅ

ረሱል (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም)

## (ዱዓ ዒባዳ ነው)

ብለዋል

# የዱዓ ሥነ ሥርዓት

- ለሰው ዱዓ ከማድረግ በፊት መጀመርያ ለራስ ዱዓ ማድረግ
  ምሳሌ :- አላህ ሆይ ማረኝ እከሌንም ማረው ማለት።
- አላህን ባማሩ ስሞቹና በላቁ ባሕርያቱ አማላጅነት ዱዓ ማድረግ ወይንም ዱዓ የሚያደርገው ሰው እራሱ የሰራውን ኸይር ሥራ አስታውሶ እየጠቀሰ ዱዓ ማድረግ ወይንም በሕይወት ባለና አጠገብ በሚገኝ ሷሊህ ሰው ዱዓ ማስደረግ።
- የሚበሉት የሚጠጡትና የሚለብሱት ሁሉ ሐላል መሆን አለባቸው።
- ዝምድናን በመቁረጥ ወይንም ወንጀል በሆኑ ነገሮች ዱዓ ያለማድረግ።
- ዱዓ የሚያደርግ ሰው በመልካም እያዘዘ ከመጥፎ የሚከለክልና ከወንጀል የራቀ መሆን አለበት።

## ዱዓ ተቀባይነት ያለባቸው ወቅቶች

- በምሽት ላይ
- ከሰላቶች በኋላ
- ከአዛንና ከኢቃም መካከል ባለው ጊዜ
- በተለይ በመጨረሻ ሊሶ ሌሊት
- ዝናብ በሚጥልበት ጊዜ
- በጁምዓ ዕለት በመጨረሻው ክፍለ ጊዜ
- ከእውነተኛ ኒያ ጋር የዘምዘም ውሃ ሲጠጣ
- በሱጁድ ወቅት

## ዱዓ ተቀባይነት ያለባቸው ወቅቶች

- ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ ዱዓ ሲያደርግ
- የዓረፋ ቀን የሚደረግ ዱዓ
- ሙስሊሞች በተሰባሰቡበት የዳዕዋ ቦታ
- የመንገደኛ ዱዓ
- ሷሊሕ ልጅ ለወላጆቹ የሚያደርገው ዱዓ
- ከውዱዕ በኋላ በሱና የሚደረግ ዱዓ
- ትንሹ ጀመራት ላይ ጠጠር ከተወረወረ በኋላ
- መካከለኛው ጀመራት ላይ ጠጠር ከተወረወረ በኋላ
- ካዕባ ውስጥ የሚደረግ ዱዓ (ሂጅር የሚባለው ክልል ውስጥ የሰገደ የካዕባው ውስጣዊው ክልል ነው)
- የሰፋ ኮረብታ ላይ የሚደረግ ዱዓ
- የመርዋ ኮረብታ ላይ የሚደረግ ዱዓ
- ሙዝደሊፋ መሽዓረል - ሐረም ላይ የሚደረግ ዱዓ

**ሙስሊም ያለአንዳች ጥርጥር ምንግዜም የትም ቦታ ቢሆን ከዱዓ መለየት የለበትም**

– ጥራት የተገባው አላህ ለባርያው በጣም የቀረበ መሆኑን በቁርአን ሲገልፅ :-

وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌ أُجِيبُ دَعْوَةَ الدَّاعِ
إِذَا دَعَانِ فَلْيَسْتَجِيبُوا لِي وَلْيُؤْمِنُوا بِي لَعَلَّهُمْ يَرْشُدُونَ ﴿١٨٦﴾

ትርጉም ((ባሮቼም ከኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው) :- እኔ ቅርብ ነኝ የለማኙንም ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ በኔም ይመኑ እነሱም ሊመሩ ይከጀላልና::)) አል በቀራህ 186

ነገር ግን በዱዓ የተለየ ወቅት ፣ ጊዜና ፣ ሁኔታን መምረጥ የተሻለ ነው

# የተመረጡ ዱዓዎች

በዓረፋ በሙዝደሊፋ እና በሌሎችም ቦታዎች የሚደረጉ ተስማሚ ዱዓዎችና ሌሎችም እንዳመችነቱ የሚደረጉ ዱዓዎች::

**አላህ ሆይ** በሐይማኖቴ በዓለማዊ ሕይወቴ በቤተሰቤ እና በንብረቴ ሰላምና ምህረት እጠይቅሃለሁ::
አላህ ሆይ ገበናዬን ሸፍንልኝ ፣ ከፍርሃት አረጋጋኝ አላህ ሆይ ከፊት ለፊቴ ፣ ከበስተኋላዬ ፣ ከበስተቀኜ ፣ ከበስተግራዬ ፣ እና ከበስተላዬ ጠብቀኝ ፡፡ ከበስተታቼም ከሚገጥመኝ እንከን በሀያልነትህ እጠበቃለሁ ፡፡

**አላህ ሆይ** ለአካላቴ ጤና ስጠኝ ፣ አላህ ሆይ ፡- ለመስማዬ ጤና ስጠኝ ፣ አላህ ሆይ ፡- ለማይብት ጤና ስጠኝ ፣ ከአንተ በስተቀር ጌታ የለም ፡ አላህ ሆይ ፡- አንተ ጌታዬ ነህ ከአንተ በስተቀር ጌታ የለም የፈጠርከኝ አንተ ነህ እኔ ባርያህ ነኝ ፡፡
አላህ ሆይ እኔ የቻልኩትን ያህል ላንተ ልገዛ በገባሁት ቃልና አደራህን በማክበር ላይ ነኝ ከሰራሁት ወንጀል በአንተ እጠበቃለሁ የዋልክልኝ ፀጋ ከአንተ መሆኑን አምናለሁ ፣ በሰራሁትም ወንጀል አምናለሁ ማረኝ ወንጀልን ከአንተ በስተቀር ማንም አይምርምና ፡፡
አላህ ሆይ ፡- ከሃዘንና ከጭንቀት በአንተ እጠበቃለሁ ፡ በዕዳ ተሸንፎ (ተዘፍቆ) በአስጨናቂ ወንድ ከመሰቃየት በአንተ እጠበቃለሁ ፡፡
አላህ ሆይ ፡- ይህንን ቀን መጀመርያውን አስተካክለው ፣ መሐከሉን መልካም ዕድል ያለበት አድርገው ፣ መጨረሻውን የተዋጣለት አድርገው ፡፡ አንተ አዛኝና ሩሕሩሕ ሆይ በዱንያም ሆነ በአኺራ መልካሙን እጠይቅሃለሁ ፡፡

**አላህ ሆይ** የፈረድከውን እንድወድ ፣ ከሞት በኋላ እንድደሰትና ወደ ተከበረው ፊትህ በማየት እንድረካ ፣ ካንተ መገናኘትን እንድናፍቅ እጠይቅሃለሁ ፡፡ ጌታዬ ፡- ከሚጎዳ ጠላት ፣ ከሚያጠም ፈተና ጠብቀኝ ፡ ጌታዬ ፡- እንዳልበድልም እንዳልበደልም ፣ ድንበር እንዳልጥስም እንዳይጣስብኝም ፣ ምሕረት የሌለው ስህተትና ወንጀል ከመስራት በአንተ እጠበቃለሁ::

# ዱዓ ማለት ዒባዳ ነው

**አላህ ሆይ** በዕድሜ መግፋት የጃጀ እንዳልሆን በአንተ እጠበቃለሁ ። አላህ ሆይ ፦ ለተሻለ ሥራና ፀባይ ምራኝ ወደ ተሻለው ከአንተ በስተቀር ማንም አይመራም ፡ መጥፎውን አስወግድልኝ መጥፎውን ከአንተ በስተቀር ማንም አያስወግድም ።

**አላህ ሆይ** በሃይማኖቴ አስተካክለኝ ፣ ቤቴን አስፋልኝ ፣ ሲሳዬን ባርክልኝ ፡ ጌታዬ ፦ ከችግር ፣ ከመዘናጋት ፣ ከውርደትና ከመናጢነት በአንተ እጠበቃለሁ ። ጌታዬ ሆይ ከክህደት ፣ ከማፈንገጥ ፣ ከጥመት ከይስሙልኝ እና ከይዩልኝ በአንተ እጠበቃለሁ ። ጌታዬ ሆይ፦ መስማት ከመሳን ፣ ከዲዳነት ፣ ከቁምጥናና ከመጥፎ በሽታዎች በአንተ እጠበቃለሁ።

**አላህ ሆይ** ለነፍሴ አንተን ፍራቻ ስጣት አጥራትም አንተ የተሻልክ አጥሪ ነህና ፡ አንተ የነፍሴ የበላይዋ እና ጌታዋ ነህ ። አላህ ሆይ ፦ ከማይጠቅም ዕውቀት ፣ አንተን ከማይፈራ ልቦና ፣ ከማትጠግብ ነፍስ ፣ ተቀባይነት ከሌለው ዱዓ በአንተ እጠበቃለሁ ።

**አላህ ሆይ** ከሠራሁት መጥፎም ሆነ ካልሰራሁት መጥፎ በአንተ እጠበቃለሁ ፡ አላህ ሆይ ፦ ፀጋህ እንዳይርቀኝ ፣ ጤናዬ እንዳይቀየር ፣ ከድንገተኛ ብቀላህ ፣ ከሁሉም ቅጣትህ በአንተ እጠበቃለሁ ።

**አላህ ሆይ** ከእልቂት ፣ ከማሽቆልቆል ፣ ከመጥለቅለቅ ፣ ከቃጠሎና ከእርጅና በአንተ እጠበቃለሁ ።

– ጌታዬ ሆይ ፦ ሞት ሲመጣብኝ ሸይጣን እንዳይጠጋኝ በአንተ እጠበቃለሁ ። ጌታዬ ሆይ ተነድፎ ከመሞት በአንተ እጠበቃለሁ ። ጌታዬ ሆይ ከማይለቅ ስግብግብነት በአንተ እጠበቃለሁ።

# የተመረጡ ዱዓዎች

**አላህ ሆይ** ከመጥፎ ፀባይ ፣ ሥራ ፣ ፍላጎትና በሽታ በአንተ እጠበቃለሁ ፡ ጌታዬ ሆይ በዕዳ ጫና ከአስጨናቂ ወንድ ፣ በጠላት ከመዋረድ በአንተ እጠበቃለሁ ።

**አላህ ሆይ** ሃይማኖቴን አብጅልኝ ለጉዳዬ ሁሉ መከታዬ ነውና ፣ ዱንያዬን አብጅልኝ መኖርያዬ ነውና ፣ አኺራዬን አብጅልኝ መመለሻዬ ነውና ፣ የሕይወት ዘመኔ መልካሙን ሁሉ የሚጨምር አድርገው ሞቴን ከሁሉም ሸር የሚያሳርፈኝ አድርገው ፣ ጌታዬ ሆይ እርዳኝ ተቃዋሚዬን እንዳትረዳ ፣ ደግፈኝ ተቃዋሚዬን እንዳትደግፍ ። ጌታዬ ምራኝ ስትመራኝም ገር አድርግልኝ ።

**አላህ ሆይ** አንተን የሚያስታውስ ፣ አንተን የሚያመሰግን ፣ ትዕዛዝህን የሚቀበል ዘወትር ለአንተ የሚታዘዝ ፣ ሁሌ ወደ አንተ ተመላሽ ፣ አድርገኝ ፦ ጌታዬ ፦ ተውበቴን ተቀበል ሀጢያቴን እጠብልኝ ፣ ልመናዬን ተቀበል ፣ ዋቢዬን (መመርያዬን) አፅናልኝ ፣ ልቦናዬን አቅናልኝ ፣ አንደበቴን አስተካክለው ፣ በልቤ ያለውን ተናዳጅነት አስወግድልኝ ።

**አላህ ሆይ** በአቋሜ እንድፀና ፣ በትዕዛዝህ ላይ ቆራጥ እንድሆን እጠይቅሃለሁ ። ጌታዬ ሆይ ፦ በሰጠኸኝ ፀጋ እንዳመሰግን ፣ ላንተ መገዛትን እንዳሳምር እጠይቅሃለሁ ። ጌታዬ ሆይ ፦ ሰላማዊ ልቦና ፣ እውነተኛ አንደበት ፣ እጠይቅሃለሁ ፡ ጌታዬ ሆይ አንተ ከምታውቀው ጥሩ ነገር እጠይቅሃለሁ ፣ ሸርነቱን ከምታውቀው ነገር በአንተ እጠበቃለሁ ፣ አንተ በምታውቀው ሁሉ ምህረት እጠይቅሀለሁ አንተ የተሰወረን አዋቂ ነህና።

**አላህ ሆይ** መንገዴን አሳውቀኝ ፣ ከነፍሴ ሸር ጠብቀኝ ፣ አላህ ሆይ ፦ መልካም ሥራ እንድሰራ መጥፎን ሥራ እንድተው ድሆችን እንድወድ ፣ እንድትምረኝና እንድታዝንልኝ እጠይቅሃለሁ ፡ ጌታዬ ሆይ ፦ ባሮችህን ለመፈተን ስትፈልግ ከሚፈተኑት አታድርገኝ ወደ አንተም ውሰደኝ ።

**አላህ ሆይ** ውዴታህን ፣ አንተን የሚወዱትን ውዴታ ፣ ወደ አንተ ውዴታ የሚያቃርቡ ሥራዎችን እጠይቅሃለሁ ፡ አላህ ሆይ ፦ የተሻለውን ጥያቄ ፣ የተሻለውን ፣ ዱዓ ፣ የተሻለውን ውጤት ፣ የተሻለውን ምንዳ ፣ እጠይቅሃለሁ ። ጌታዬ ፦ በኢማኔ ፅኑ አድርገኝና ሚዛኔን አክብደው ፣ እማኝነቴን አረጋግጥልኝ ፣ ደረጃዬን ከፍ አድርገው ፣ ሰላቴንና ኢባዳዬን ተቀበለው ፣ ስህተቴን ማረኝ ። ጌታዬ ፦ ከፍ ያለውን የጀነት ደረጃ እጠይቅሃለሁ ።

# ዱዓ ማለት ዒባዳ ነው

**አላህ ሆይ** መክፈቻውም ማጠቃለያውም ሁለመናው ያማረውን መጀመርያውም መጨረሻውም ውጩም ውስጡም ያማረውን ከፍ ያለውን የጀነት ደረጃ እጠይቅሃለሁ ።

**አላህ ሆይ** አንተን ማወደሴን ከፍ እንድታደርገው ፣ ወንጀሌን እንድታራግፍልኝ ፣ ልቤን እንድታጠራልኝ ፣ ነውሬ (አውረቴ) እንዲጠበቅ ፣ ወንጀሌን እንድትምረኝ እጠይቅሃለሁ ።

**አላህ ሆይ** መስሚያዬን ፣ የማይበትን ፣ ፀባዬን ፣ ቤተሰቤን ሕይወቴን ፣ ሥራዬን እንድትባርክልኝና መልካም ሥራዬን እንድትቀበለኝ እጠይቅሃለሁ ። ከፍ ያለውን የጀነት ደረጃ እጠይቅሃለሁ ። አላህ ሆይ ፡- ከአስጨናቂ ፈተና ፣ ከዘቀጠ ጥመት ፣ ከመጥፎ ውሳኔህ ፣ በጠላት ከመዋረድ በአንተ እጠበቃለሁ ። አላህ ሆይ ፡- አንተ ልብን ገለባባጭ የሆንክ ጌታ ልቤን በሃይማኖትህ የፀና አድርገው ። አላህ ሆይ ፡- አንተ ልብን የምትመራ ጌታ ልባችንን በትዕዛዝህ ላይ ምራት ።

**አላህ ሆይ** ጨምርልን እንጂ እንዳትቀንስብን ፣ ለግሰን እንጂ ፣ አትንሳን ፣ ሥጠን እንጂ እንዳትከለክለን ፣ ምረጠን እንጂ አትምረጥብን ።

**አላህ ሆይ** ጉዳያችን በጠቅላላ በመጨረሻው ያማረ አድርገው ከዱንያ ውርደት ከአኼራ ቅጣት አርቀን ።

**አላህ ሆይ** በእኛ እና አንተን በማመፅ መካከል የሚጋርደውን ፍራቻህን ለግሰን ፣ ጀነት የሚያደርሰንን አንተን መታዘዝ ስጠን ፣ በዱንያ የሚገጥመንን ችግር የምናቀልበትን ጥርጥር የሌለውን እምነት ስጠን ፣ በሕይወት እስካለን በምንሰማበት በምናይበትና በጉልበታችን እጠቃቅመን ይህንኑ ለወራሾቻችን አድርገው ፣ ብቀላችንን በበደሉን ላይ ብቻ አድርገው ፣ በጠላቶቻችን ላይ ድል አቀናጀን ፣ ዱንያን ትልቁ ጭንቃችንና የዕውቀታችን መጨረሻ አታድርገው ፣ የሚገጥመንን አደጋ በዲናችን ላይ አታድርገው ፣ በወንጀላችን ሰበብ አንተን የማይፈሩ ለኛ የማያዝኑትን አትሹምብን።

# የተመረጡ ዱዓዎች

**አላሀ ሆይ** ወደ እዝነትህ የሚያቃርብ ሥራ ፣ ቅርብ ምህረትህን ፣ ከበጎ ነገር ሁሉ መጠቀምን ፣ ከወንጀል ሁሉ መራቅን ፣ በጀነት ማሸነፍን ፣ ከእሳት መጠበቅን ፣ እጠይቅሃለሁ ።

**አላሀ ሆይ** ወንጀላችንን ሳትምረን ፣ ነውራችንን ሳትሸፍንልን ፣ከጭንቃችን ሳትገላግለን ፣ ብድራችንን ሳትከፍለው ፣ በዱንያም ሆነ በአኺራ አንተ የምትወደውና ለኛ የሚጠቅመንን ጉዳያችንን ሳታሳካው እንዳትተወን ፣ አንተ የአዛኞች አዛኝ ነህና ።

**አላሀ ሆይ** ከአንተ በሆነ እዝነትህ ልቤን እንድትመራው ፣ ጉዳዬን እንድታጠናክርልኝ ፣ የባከነውን እንድትሰበስብልኝ ፣ የራቀኝን እንድትጠብቅልኝ ፣ የፊትለፊቴን ከፍ እንድታደርግልኝ ፣ ፊቴን እንድታፊካልኝ ፣ ሥራዬን እንድታጠራልኝ ፣ መንገዴን እንድታመላክተኝ ፣ የሚመጥብኝን ፈተና እንድትመልሰው ፣ ከሁሉም ሸር እንድትጠብቀኝ እጠይቅሃለሁ።

**አላሀ ሆይ** የፍርዱን ቀን ማሸነፍ ፣ በተድላ መኖር ፣ የሸሂዶችን ደረጃ ፣ ከነብያቶች መቆራኘት ፣ ጠላትን ድል መንሳት እጠይቅሃለሁ ።
– አላሀ ሆይ ፦ በኢማኔ ላይ ጤና ፣ በመልካም ፀባይ ላይ ኢማን ፣ ድል የሚያስከትል ስኬት ፣ ከአንተ የሆነ እዝነት ፣ ከአንተ የሆነ ሰላም ፡ ምህረትና ውዴታህን እጠይቅሃለሁ።

**አላሀ ሆይ** ጤናና ምህረትህን ፣ ያማረ ፀባይና በፈረድከው ወዶ መቀበልን እጠይቅሃለሁ ፤ አላሀ ሆይ ከነፍሴ ሸር ፣ በቁጥጥርህ ሥር ባሉ ተንቀሳቃሾች ሸር ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ ። ጌታዬ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ነው

**አላሀ ሆይ** ንግግሬን ትሰማለህ ፣ ያለሁበትን ታያለህ ፣ ሚስጥሬንም ገሃዬንም ታውቀዋለህ ፣ ከጉዳዬ ካንተ የሚደበቅ ትንጣት ታክል የለም ፣ እኔ አላዛኝ ፈላጊ ፣ ተረጂና ተጠጊህ ፣ ወንጀለኛና ፈሪህ ፣ ሁሌ ወንጀሉን የሚያምን ነኝ ። ጌታዬ የምስኪን አለማመን እለምንሃለሁ ፣ የወንጀለኛ የተዋረደ በጣም የፈራን የተጎዳ ሰው አለማመን እለምንሃለሁ ፣ አንገቱን አቀርቅሮ ሰውነቱን አዋርዶ ባፍንጫው የተደፋ ሰው ልመና እለምንሃለሁ።

# ዱዓ ማለት ዒባዳ ነው

## የተሳፋሪ ዱዓ

بسم الله ، الحمد لله

سُبْحَٰنَ ٱلَّذِى سَخَّرَ لَنَا هَٰذَا وَمَا كُنَّا لَهُۥ مُقْرِنِينَ ﴿١٣﴾ وَإِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا لَمُنقَلِبُونَ ﴿١٤﴾

الحمد لله ، الحمد لله ، الحمد لله    الله أكبر ، الله أكبر ، الله أكبر ،

سبحانك اللهم إني ظلمت نفسي فاغفر لي فإنه لا يغفر الذنوب إلا أنت

## የመንገደኛ ዱዓ

الله أكبر ، الله أكبر ، الله أكبر

سُبْحَٰنَ ٱلَّذِى سَخَّرَ لَنَا هَٰذَا وَمَا كُنَّا لَهُۥ مُقْرِنِينَ ﴿١٣﴾ وَإِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا لَمُنقَلِبُونَ ﴿١٤﴾

اللهم إنا نسألك في سفرنا هذا البر والتقوى ، ومن العمل ما ترضى اللهم هون علينا سفرنا هذا واطوعنا بعده ، اللهم أنت الصاحب في السفر والخليفة في الأهل ، اللهم إني أعوذ بك من وعثاء السفر وكآبة المنظر وسوء المنقلب في المال والأهل

وإذا رجع قالهن وزاد فيهن: آيبون، تائبون، عابدون، لربنا حامدون

## ሩክነል የማኒና ሐጀረል አስወድ መካከል የሚደረግ ዱዓ

رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِى ٱلْءَاخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿٢٠١﴾

## ሰፋና መርዋ ኮረብታዎች ላይ ተቁሞ የሚደረግ ዱዓ

لما دنا ﷺ من الصفا قرأ ﴿ إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلْمَرْوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِ ﴾

أبدأ بما بدأ به الله .. فبدأ بالصفا ..

فصعد عليه حتى رأى البيت فاستقبل القبلة، فوحد الله وكبره وقال

لا إله إلا الله وحده لا شريك له ، له الملك وله الحمد وهو على كل شيء قدير ، لا إله إلا الله وحده ، أنجز وعده ، ونصر عبده وهزم الأحزاب وحده

ثم دعا بين ذلك . قال مثل هذا ثلاث مرات وفعل على المروة كما فعل على الصفا .

# የተከበራችሁ ሐጃጆች

እንተ ከሩቅና ከስምጥ ሸለቆ አቋርጠህ የመጣህ ሐጅ ሆይ

ይህ ሐጅ የተሟላ እንዲሆን ትልቅ ምንዳ እንድታገኝበት ወንጀልህ እንዲማር ጥፋትህ እንዲሰረዝ ደረጃህ ከፍ እንዲል አላህ በኪታቡ ባዘዘውና ነብዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በሱናቸው ባመላከቱት መሠረት በተሟላ መልኩ መከናወን አለበት፡፡ ሐጁም የተጠበቀ እንዲሆን ከተከለከሉ ነገሮች ፣ ከማፈንገጥ ፣ ከጭቅጭቅና ከሁሉም ወንጀል መራቅ ያስፈልጋል ፡፡

ምንዳው ጀነት የሆነው ሐጀል መብሩር ለማግኘት የሐጅ ደንቡና ግዴታው ተጠብቆ ከሁሉም ወንጀል ነፃ ሆኖ ወደ መልካምና ጥሩ ሥራ የሚገፋፋ መሆን አለበት ፡፡

ዓሊሞች እንደሚሉት ሐጀል መብሩር ማለት በሐጅ ወቅት አላህ ወንጀል ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ የተከለከለ ማለት ነው ይላሉ ፡፡


ስለዚህ እኛ ለዚህች አማኝ ሕይወትህ የምንመኝልህ በሃያሉ አላህ ቁርአን ተመርተህ በመልክተኛው ሙስጠፋ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ሱና ተዳኝተህ አጠገብህ ላጥለቀለቁህ ሙስሊሞች ምሳሌ በመሆን ከሐጃጆች ጋር ያለህ አቀራረብ ፍፁም ወንድማዊ መሆን አለበት፡፡

በመጨረሻም በአላህ ፈቃድ ሐጅህም የተዋጣለት (መብሩር) ድካምህም የሚያስመሰግንህ (መሽኩር) እንዲሆን ወደ ቤተሰቦችህም እናትህ እንደወለደችህ ቀን ንፁህ ሆነህ ወንጀልህ ተምሮ እንድትመለስ እንመኛለን፡፡

ሐጅ አድርገህ ወደ ሃገርህ ስትመለስ ነፍስህ አላህ ወደጠላው ወንጀል በጠራችህ ቁጥር የሚከተሉትን አስታውስ ፡-

– በካዕባ ዙርያ ስትጠውፍና ሰፋ መርዋ ስትመላለስ አስታውስ
– ዓረፋ በቆምክበት ቀን ከአላህ እዝንትና ምህረት እየተመኘህ ያደረግከውን ዱዓ አስታውስ፡፡

ምናልባት እነዚህ ትውስታዎች ወንጀል ከመስራትና በአላህ ላይ ከማመፅ ይከለክሉህ ይሆናል ፡፡



ሁሉንም መወሰን ለሚችለው አላህ የሁሉንም ሐጅ መብሩር ወሰዕዩን መሽኩር እንዲያደርገው እንለምነዋለን፡፡

ወሰለሏሁ ዓላ ሰይድና መሐመድ ወዓላ አሊሂ ወሰሕቢሂ ወሰለም

# ማውጫ



| | | |
|---|---|---|
| 1 | የጉዞ ሥነሥርዓት | 8 |
| 2 | ኢሕራም | 10 |
| 3 | የኢሕራም ክልሎች | 12 |
| 4 | በኢሕራም ወቅት የሚከለከሉ ነገሮች | 14 |
| 5 | የሐጅና ዑምራ ማብራሪያ | 17 |
| 6 | የዑምራ አደራረግ | 19 |
| 7 | የሐጅ አፈፃፀም | 27 |
| 8 | የዙልሒጃ ስምንተኛው ቀን | 28 |
| 9 | የዙልሒጃ ዘጠነኛው ቀን | 30 |
| 10 | ሙዝደሊፋ | 32 |
| 11 | ዙልሒጃ አሥረኛው ቀን | 34 |
| 12 | ጠዋፈል ኢፋዳ | 36 |
| 13 | አያመል ተሽሪቅ | 37 |
| 14 | ጠዋፈል ወዳዕ | 39 |
| 15 | የሐጅ መሠረቶችና ግዴታዎች | 40 |
| 16 | ሴቶችን የሚመለከት ደንብ | 41 |
| 17 | የነብዩን (ሰ.ዓ.ወ) መስጊድ ዚያራ | 47 |
| 18 | አስፈላጊ ጥያቄና መልስ | 53 |
| 19 | ዱዓ | 67 |